
# ባልደራስ

1ኛ ዓመት ቁጥር 06 መጋቢት 28 ቀን 2013 ዓ.ም.


## ወንጀለኛው ማን ነው ?



ገጽ 12

# መንግሥታዊው የገዳ ወረራ



ገጽ 4



## ግልፅ ደብዳቤ ለአቶ ደመቀ መኮንን

‹ሰዎች ለሰዎች› የተሰኘው የጀርመኑ ተራድኦ ድርጅት በተለያዩ የኢትዮጵያ አካባቢዎች ትምህርት ቤቶችን፣ የጤና ተቋማትንና ሌሎች የመሠረተ ልማት አውታሮችን ሠርቷል:: በዚህም መሥራቹ ካርል ሄንዝ በሕዝብ ዘንድ ተወደዱ:: ታዲያ በአንድ የምርጫ ወቅት ኢሕአዴግ ‹ነፍጠኛ› እያለ ሲጨቁነው ወደ ኖረው የሸዋ አማራ የ‹ምረጡኝ› ቅስቀሳውን ይዞ ሄደ:: በወቅቱ የመርሐቤቴ ሰው ‹ካርል የሚወዳደር ከሆነ እርሱን እንመርጣለን:: ከእርሱ ውጭ ምርጫ የለንም› ማለቱን የሰማሁት እኔ ብቻ ነኝ የሚል ግምት የለኝም:: ክቡር አቶ ደመቀ መኮንን እርስዎም ሰምተው እንደሚሆን እገምታለሁ:: እንዲያውም ከእኔ ወፏ ነገረችኝ ዓይነት ወሬ ይልቅ እርስዎ በሪፖርት ደረጃ የተጠናቀረ መረጃ ከበታች ካድሬዎችዎ ደርሰዎት ይሆናል:: ኧረ እንዲያውም ...

ወደ ገጽ 14 ዞሯል

# የአማራ ሕዝብ የራሱን ጊዜያዊ አስተዳድር በማቋቋም ከተደቀነበት የመጥፋት አደጋ ያምልጥ!

ወያኔ/ትሕነግ የብሔር ፖለቲካን ለኢትዮጵያ ካስተዋወቀበት ጊዜ ጀምሮ ሌሎች አቻ ብሔሮች የራሳቸው ፖለቲካዊ ወኪል ሲኖራቸው አማራ እስከ አሁንም ድረስ በጠላቶቹ ተወክሏል:: ራሱን ኢሕዴን/ብአዴን/አዴፓ/የአማራ ብልፅግና እያለ የመጣው ቡድን ከአማራው አብራክ ባልተወለዱና የአማራው ሕዝብ ጠላቶች የተመሰረተ ነው:: ዛሬም የዚህ ቡድን መሪዎች የመሥራቾቻቸው ርዝራዦች ናቸው:: ብአዴን በአማራው ሕዝብ ስም ቢጠራም እንደ ትህነግ ሁሉ አማራውን በጠላትነት ፈርጆ በፖለቲካ ፕሮግራሙ ላይ ያሠፈረ የሞግዚት ድርጅት ነው:: ወያኔን ልክ በማስገባት እንቅስቃሴው ሕዝባዊ ወገንተኝነት ያገኘ መስሎ ቢታይም አዲሱ ጌታውን ኦሕዴድ/ብልፅግናን አደግድጎ እያገለገለ ይገኛል::

በዚህም ምክንያት አገር መስራቹ የአማራ ሕዝብ አገር አልባ ሆኗል:: ከተለያዩ ቦታዎች እየተፈናቀለ እና እየተሳደደ ይገኛል:: በተለይም ባለፉት ሰባት ወራት ውስጥ የማያባራ ጅምላ ጭፍጨፋ እየተፈፀመበት ይገኛል:: ጠቅላይ ሚንስትሩም ‹ጨፍጭፏቸው› የሚል የሥራ መመሪያ የሚሰጡ እንጂ የሕዝቡን ሕልውና የሚያስጠብቁ አይደሉም። በዚህ ሕዝብ ላይ እየተፈፀመ ያለው መንግሥታዊ ጅምላ ጭፍጨፋ በኦነጋዊው ኦሕዴድ/ብልፅግና በሰፊው የታቀደበት እንደሆነ እሙን ነው። ለዚህም በቂ ማሳያዎች አሉ::

በመሆኑም ሰፊው የአማራ ሕዝብ ከ‹ክልሉ› መስተዳድርም ሆነ ከፌዴራሉ መንግሥት መፍትሔ እንደማያገኝ አውቆ ህልውናውን ለማስጠበቅ የራሱን ጊዜያዊ ሕዝባዊ አስተዳድር ሊመሰርት ይገባል:: ከዚህ ደረጃ ላይ ለመድረስም በቅድሚያ የሚከተሉትን ተግባራት ይፈፅም ዘንድ ዝግጅት ክፍላችን ጥሪውን ያቀርባል፡-

በማያባራ ሰላማዊ ሕዝባዊ እምቢተኝነት በአገዛዙ ላይ ያለውን ተቃውሞ ለውጥ እስኪመጣ ድረስ ማሳየት አለበት::

ማንኛውም አማራ በያለበት ያገኘውን የነፍስ ወከፍ የጦር መሳሪያ ታጥቆ ራሱን ይከላከል:: ይህ ሲሆን መሳሪያውን ተጠቅሞ ሰላማዊ ሰዎችን ፈፅሞ ማጥቃት የለበትም:: ታጣቂነቱን በሕገ ወጥነት ፈርጀው ሊያሸማቅቁት የሚፈልጉ ኀዥዎቹንም መሳሪያ ታጥቆ መከላከል ዓለም አቀፍ መብት መሆኑን ይንገራቸው::

አማራው ካልተወከለበትና ካልተሳተፈበት ሕገ መንግሥት ጀምሮ ለማንኛውም መንግሥታዊ ሕግ፣ አዋጅ፣ መመሪያም ሆነ ደንብ ተገዥነቱን ያቁም:: ይልቁንስ ተገዥነቱ ለሞራሉ ይሁን:: እንደየ ሃይማኖቱ ለእምነቱ ይሁን::

ዘርን ለማስቀጠል የሚደረገውን ይህንን የህልውና ትግል በአማራው ስም ተደራጅተው በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር እየተንቀሳቀሱ ያሉ የሲቪክ ተቋማት በግንባር ቀደምነት ይመሩት ዘንድ የተገባ ነው። በተለይም በሀገር ውስጥ በየከተሞች ሰፊ አደረጃጀቶች ያለው የአማራ ወጣቶች ማህበር ሕዝባዊ እንቢተኝነቱን በማስተባበር ታሪካዊ ሓላፊነቱን ሊወጣ ይገባል:: የአማራ ምሁራን ይህንን በሃሳብ መደገፍ ይጠበቅባቸዋል:: ይህ ካልሆነ ግን አማራ የሚባል ብሔር በገዳ ወረራ እንደጠፉ ሌሎች ብሔሮች ሁሉ መጥፋቱ አይቀሬ ነው:: በቤንሻንጉል ጉምዝ እየተደረገ ያለው ጅምላ ጭፍጨፋም ኦሕዴድ የከፈተው የውክልና ጦርነት እንደሆነ ሊታወቅ ይገባል:: ፈጣሪ የሰማዕት አማራዎችን ነፍስ ይማር! ለመላው አማራ መፅናናትን እንመኛለን::


**ባልደራስ ጋዜጣ**
መስከረም 1 ቀን 2013 ዓ.ም.
ተመሰረተ

በየ15 ቀኑ የሚታተም

**አሳታሚ**
ባልደራስ ለእውነተኛ ዴሞክራሲ ፓርቲ (ባልደራስ)

**ዋና አዘጋጅ**
ጌጥዬ ያለው
ክፍለ ከተማ:- ቂርቆስ
ወረዳ:- 02 የቤት ቁጥር:- አዲስ
ስልክ:- +2519 24 51 70 77
ኢ-ሜይል:- newsgett@gmail.com

**ከፍተኛ አዘጋጅ**
ወግደረስ ጤናው

**አምደኞች**
ገለታው ዘለቀ
ኢንጂነር ጌታነህ ባልቻ

**አርታዒ**
መሰበወርቅ ቅጣው
ነብዩ ውብሸት

**ፀሐፊ:-** ሕይወት ዳዊት

**የገፆች ቅንብር** ሐብ-ዲዛይን

**ገፀ ድር አስተዳደር** ኢስያስ ፅጉ

# በአማራ ላይ የደረሰውን ጅምላ ጭፍጨፋ የሚያጣራ ኮሚሽን እንዲቋቋም አምስት ተቃዋሚ ፓርቲዎች ጠየቁ

አምስቱ ፓርቲዎች ማለትም የአማራ ብሔራዊ ንቅናቄ (አብን)፣ ባልደራስ ለእውነተኛ ዴሞክራሲ ፓርቲ (ባልደራስ)፣ እናት ፓርቲ፣ የትግራይ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ (ትዴፓ) እና የኢትዮጵያ ዜጎች ለማሕበራዊ ፍትሕ (ኢዜማ) በአማራ ሕዝብ ላይ እየተፈፀመ ያለውን ጥቃት በጋራ በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ አውግዘዋል። ጥቃቱ በመንግሥት መዋቅሮች የተደገፈ እንደሆነም ጠቁመዋል። ጅምላ ጭፍጨፋው ሀይማኖትን እና ብሔርን መሰረት ያደረገ እንደሆነም ነው የገለፁት። የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የደረሰውን ጉዳት በጥልቅ መርምሮ ውጤቱን የሚያሳውቅ ገለልተኛ ኮሚሽን እንዲያቋቁምም ጠይቀዋል።

"የህዝብን ሰላምና ደህንነት በንቃት ለመጠበቅ፤ የሀገራችንን አንድነት ለማጎልበትና ዘላቂነቷን ለማረጋገጥ እኛ የፖለቲካ ፓርቲዎቹ በጽናት በጋራ ግንባር ቀደም ሆነን እንደምንሰለፍ እናረጋግጣለን" ያሉት ፓርቲዎቹ ተከታዩን ባለስምንት ነጥብ አቋም አውጥተዋል፡-

1. በሀገራችን ውስጥ በበርካታ አካባቢዎች በተለይም በኦሮሚያ ክልል እና በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ውስጥ የሚኖሩ የአማራ ተወላጆች እና በአጠቃላይ መጤ ተብለው በተፈረጁ ዜጎች ላይ በተለያዩ የሀገራችን አካባቢዎች እየተፈፀመ ያለውን ዘር ተኮር ጥቃት በጥብቅ እናወግዛለን፣
2. የፌዴራሉ መንግስትና የክልሎቹ መንግስታት ችግሩን በዘላቂነት ለመፍታት በቁርጠኝነት መንቀሳቀስ እንዳለባቸው እናሳስባለን፣
3. የችግሩን ግዝፈትና መደጋገም እንዲሁም በሀገራችን አንድነትና ደህንነት ላይ የደቀነውን ከፍተኛ አደጋ ከግምት ውስጥ በማስገባት ዘላቂ እልባት የመስጠቱ ጉዳይ እንደተጠበቀ ሆኖ የሕዝብ ተወካዬች ምክር ቤት ገለልተኛ ኮሚሽን በማቋቋም በጥልቀት መርምሮ ውጤቱንም ለህዝብ ይፋ እንዲያደርግ በአፅንኦት እንጠይቃለን፣
4. የዚህ መግለጫ አካል የሆን ፓርቲዎችም ችግሩ የሀገር አንድነት እና ደህንነት ላይ የተጋረጠው አደጋ አስቸኳይ መፍትሄ እንደሚያሻው በማመን የመፍትሄ አካል ለመሆን እና የሚጠበቅብንን ኃላፊነት ለመወጣት ቁርጠኛ መሆናችንን እንገልፃለን።
5. በመንግስት በኩል እስካሁን በተፈፀሙት ጥቃቶች ውስጥ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ በተሳተፉ ግለሰቦችና ቡድኖች ላይ እንዲሁም በተለያየ ደረጃ የሚገኙ የመንግስት አመራሮች ሆነው የመከላከል ኃላፊነታቸውን ያልተወጡና በጥቃት የተሳተፉትን በሚመለከት በፍጥነት ተገቢው የማጣራት ስራ እንዲሰራና በህግ እንዲጠየቁ እንዲደረግ እናሳስባለን፣
6. መላው የኢትዮጵያ ህዝብ በተለያዩ አሰላለፎች ውስጥ ተካትተው ዘርና እምነት ተኮር ጥቃቶችን የሚፈፅሙ አካላትን ለማውገዝ፣ ለማጋለጥ፣ እና ለመከላከል ብሎም ለማሸነፍና በህግ ጥላ ስር ለማዋል በአንድነት እንዲቆሙ ጥሪያችንን እናቀርባለን፣
7. በተለያዩ የዓለማችን ክፍሎች የምትኖሩ ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን በሙሉ በአማራ ህዝብ ላይ በጥላቻ ሀይሎች እየተፈፀመ ያለውን ዘር ተኮር ጥቃት ለማውገዝ፣ ለማጋለጥና ለፍርድ ለማቅረብ ያለምንም ልዩነት በጋራ እንድትሰለፉ ጥሪያችንን እናቀርባለን፣
8. በተፈፀሙባቸው ጥቃቶች ምክንያት ደጋፊ ወገኖቻቸውን ላጡና በጅምላ ተፈናቅለው ችግር ላይ ለወደቁት ወገኖች በአስቸኳይ የነፍስ አድንና የመልሶ ማቋቋም የተቀናጀ ርብርብ እንዲደረግ ጥሪያችንን እናስተላልፋለን።

በአዲስ አበባ፤ ራስ አምባ ሆቴል በተሰጠው ጋዜጣዊ መግለጫ የአራቱ ፓርቲዎች የሕዝብ ግንኙነት ሓላፊዎች የተገኙ ሲሆን የትዴፓ ተወካዮች አልተገኙም። በጋራ አቋሙ እንደሚያምኑ እና በጊዜ እጥረት እንዳልተገኙም ተነግሯል። ትዴፓ በተቃዋሚ ፓርቲነት የተመዘገበ ቢሆንም በትግራይ በተቋቋመው አዲስ መንግሥታዊ መዋቅር ውስጥ አመራሮቹ ከፍተኛ የመንግሥት የሥልጣን ቦታዎች ላይ ተሰይመዋል። ፕሬዚደንቱ ዶ/ር አረጋዊ በርሀም ቀደም ብለው በጠቅላይ ሚኒስትር አብይ አሕመድ የአባይ ግድብ ማስተባበሪያ ፅ/ቤት ሓላፊ ተደርገው መሾማቸው ይታወሳል።

በመግለጫው የተገኘው ኢዜማ በበኩሉ በፅሁፍ የቀረበውን መግለጫ ቃል በቃል እንደሚያምንበት ገልፆ ይህንን ተከትሎ በመግለጫው ላይ ከየፓርቲዎቹ የተሰጡ ትንታኔዎችን እንደማይቀበል አስታውቋል።

# በወለጋ ከተገደሉት መካከል የሰባት ሰዎች አስክሬን ጠፋ

በኦሮሚያ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ ዞን አቢ ደንጉሮ ወረዳ ዳቢስ ቀበሌ ባለፈው የካቲት 27 ቀን 2013 ዓ.ም. ከተገደሉት 29 ሰዎች መካከል የ7ቱ አስክሬን አለመገኘቱን የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ጉባኤ (ኢሰመጉ) አስታውቋል። ግድያው በአማራ ተወላጆች ላይ ያነጣጠረ ቢሆንም ኢሰመጉ መጋቢት 7 ቀን 2013 ዓ.ም. ባወጣው ጥናታዊ ሪፖርት ሸፋፍኖት አልፏል። ግድያው ከምዕመናን በተጨማሪ ካህናትንም ያካተተ እንደሆነ፤ ብሎም በቤተክርስቲያን ውስጥ የተፈፀመ መሆኑን የገለፀው ሪፖርቱ ሃይማኖት ተኮር ጅምላ ጭፍጨፋ መሆኑን ግን አልገለፀም።

በጠበቃ አምሀ መኮንን የሚመራው ኢሰመጉ የሟቾች ቁጥር በእጥፍ ሊጨምር እንደሚችልም ጠቁሟል። የ22 ሰዎች የቀብር ስነ ስርዓት የካቲት 29 ቀን 2013 ዓ.ም. በአቢ ደንጉር ወረዳ ባለ እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ተፈፅሟል። በአንፃሩ የቀሪዎቹ አስክሬን በፍለጋ ላይ እንደሆነ የገለፀው ሪፖርቱ ስለ ዝርዝር አፈላለጉ አላብራራም። አስክሬኖች የሚፈለጉት በማን፣ የት እና እንዴት እንደሆነ አልገለጸም።

በተመሳሳይ በደቡብ ኢትዮጵያ አማሮ ልዩ ወረዳ ስድስት ሰዎች መገደላቸውን ጉባኤው አስታውቋል። ከሟቾች መካከል የወረዳው የገዥው ፓርቲ ሓላፊ ይገኙበታል። የወረዳውን ምክትል አስተዳዳሪ ጨምሮ ሌሎች ስድስት ሰዎች የአካል ጉዳት ደርሶባቸዋል።

ይህኛው ግድያም በአማራ ተወላጆች ላይ ያተኮረ የዘር ፍጅት እንደሆነ መንግሥታዊ ያልሆኑ የሀገር ውስጥና የውጭ ድርጅቶች ሲገልፁ ቆይተዋል። ይሁን እንጂ ግድያው የሰብዓዊ መብት ጥሰት እንደሆነ ከመግለፅ ውጭ በአማራ ላይ ያነጣጠረ ጅምላ ጭፍጨፋ መሆኑን መንግሥታዊው የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ አልገለፀም። በአንፃሩ ግድያው የማያባራ እንደሆነ አስጠንቅቋል።

"ኢትዮጵያ ተቀብላ ባፀደቀቻቸው ዓለም አቀፍ እንዲሁም አህጉራዊ የሰብዓዊ መብቶች ስምምነቶች በሕገመንግሥቱ ላይ እውቅና ያገኙት በሕይወት የመኖር፣ የአካል ደህንነትና ነፃነት መብቶች ላይ ማቆሚያ የሌለው ጥሰት እየተፈፀመ ነው። መንግሥት እነዚህን መብቶች የማክበር፣ የማስከበር እንዲሁም መብቶቹ እንዲጠበቁ አስፈላጊ ሁኔታዎችን የማሟላት ግዴታውን በሚጠበቀው መጠን እየተወጣ አይደለም" ብሏል ሪፖርቱ።

የተጠቀሱትን ግድያዎች የፈፀመው መንግሥት ኦነግ ሸኔ የሚለውና ራሱን የኦሮሞ ነፃነት ሰራዊት ብሎ የሚጠራው የሽብር ቡድን እንደሆነ ኢሰመጉ አትቷል። በቡድኑ ላይ መንግሥት የማያዳግም ርምጃ እንዲወስድም ጠይቋል።

በአንፃሩ የአብይ አህመድ መንግሥት የዚህ ቡድን ደጋፊ እንደሆነ የፖለቲካ ተንታኞች ይገልፃሉ። በማስረጃነት ከሚያነሷቸው ጉዳዮች መካከልም ቡድኑ ኤርትራ በረሀ በነበረበት ጊዜ የዛሬው ጠቅላይ ሚንስትር አብይ በብሔራዊ መረጃና ደህንነት መሥሪያ ቤት ውስጥ ሆነው በሰላይነት ያገለግሉት እንደነበር መናገራቸው ነው። ጠቅላይ ሚንስትሩ ይህንን በሕዝባዊ ውይይቶች የተናገሩት ሲሆን ሰሞኑን በተሰራጨው መፅሐፋቸውም ደግመውታል።

# መንግሥታዊው የገዳ ወረራ



**ስንታየሁ ቸኮል፣**
**ከቃሊቲ ወህኒ ቤት (የህሊና እስረኛ))**

ሰኔ 22 ቀን 2012 ዓ.ም. የአክቲቪስት አጫሉ ሁንዴሳ ግድያ ከተሰማ በኋላ በሀገራችን ኢትዮጵያ በርካታ ችግሮች ተከስተዋለል:: አምባገነኑ የአብይ አሕመድ ቡድን ክስተቱን ተገዳዳሪዎቹን ሁሉ የመደብደቢያ ዱላ አድርጎታል:: ባለፉት ሰባት ወራት ፖለቲካዊ አሰላለፎች እንዳልነበር ሆነዋል:: ዜጎች ማሕበራዊ ረፍት አጥተዋል:: ዐማራዎች በየቦታው እየታደኑ እንደ አውሬ መታረዳቸው እጅግ ተባብሶ ቀጥሏል:: መንግሥት ተብየውም አራጅ፣ አሳራጅ ሆኗል:: ፖለቲካዊ ውጥንቅጡ በዐማራ ደም እየዋኘ ወደ 6ኛው ሀገራዊ ምርጫ እየቀዘፈ ነው:: መሄጃ ያጣ የስቃይ ድምፅ ከጉራ ፈርዳ እስከ ምዕራብ ኦሮሚያ፣ ከመተከል እስከ ማይካድራ ይጮሃል:: የሚሰማው ግን የለም:: አብረን እንዳንጮህ እንኳን መጮህም ተነፍገን በእስር ቤት እንገኛለን:: ለዚህም ነው በአምባገነኖች የሀሰት ክስ ሀቀኛ ታጋዮች ከታሠርንበት ቃሊቲ ወህኒ ቤት ውስጥ ታጉሬ ይህንን ትንሽ መጣጥፍ የምሞነጫጭረው:: ብቻ ዐማራነት የሞት ቅጣት የሚያስከትል ያልተፃፈ ወንጀል ሆኗል:: ደሙ እንደ አባይ ወንዝ ሀገር አቋራጭ ማዕበል ሆኗል:: ከኢትዮጵያም አልፎ እንደ አባይ ግብፅ፣ ካይሮ ድረስ ይፈሳል:: አረንጓዴ፣ ቢጫ፣ ቀይ ሰንደቃላማ ይዘው የተገኙ ዐማራዎች በዚያው በሚገኙ የኦነግ የመገንጠል አርማ አውለብላቢዎች ጥቃት ተፈፅሞባቸዋል:: ይህ ሕዝብ ድሮም ኢትዮጵያን ያቆማት ደሙን አፍስሶ እንደነበር ስናስታውስ ታሪክ ያፅናናል:: የኢትዮጵያ የድል ችቦ የሚያበራበት ጊዜ ቅርብ እንደሆነም አምናለሁ:: በዐማራ ላይ እየደረሰ ያለው የጅምላ ጭፍጨፋ አዋጅ የኦሕዴድ/ብልፅግና የትግል አልፋና ኦሜጋ ነው:: የአዋጁ ደራሲ ጃዋር መሐመድ ብሎም አስፈፃሚዎቹ ሽመልስ አብዲሳ፣ ታከለ ኡማ እና አዳነች አቤቤም የኦሕዴድ/ብልፅግና ቼጉቬራዎች ናቸው:: ታላቁ የጥቃት ማዕከላቸው ደግሞ አዲስ አበባ ነው::

### አዲስ አበባን እንደ ወልቃይት

የወያኔ የጥቃትና የጥቅል ጥቅም (ልዩ ጥቅም ገላጭ አልመሰለኝም) ማዕከላት ወልቃይት፣ ጠለምትና ራያ ነበሩ:: መተከል፣ ደራ እና አዲስ አበባም የውክልና ማጥቂያ ማዕከላቱ ነበሩ:: ተረኛው ኦሕዴድ/ብልፅግና ደግሞ አዲስ አበባን የጥቅል ጥቅም ማዕከሉ፣ ቤንሻንጉል/ጉምዝን ደግሞ የውክልና ማጥቂያ ማዕከሉ አድርጎ ቀጥሏል:: በሀገራችን ጫፍና ጫፍ የሚሰሙ የጭፍጨፋ መርዶዎችን ወደ መሀል ሀገር ለመሳብ እየሠራ ነው:: አዲስ አበባን እንደ ትንሽ ጉብታ ንዶ ለማፍረስ ተነስቷል:: ይህንንም የሚያደርገው በወያኔ የከፋፍለህ ግዛ ሕገ መንግሥታዊ ቅሪት ነው:: አዲስ አበባን የቀውስ ሜዳ ለማድረግ እየሠራ ነው:: ባልደራስን ጨምሮ የሕጋዊ ድርጅቶችን ስም በመጥቀስ ፎቶ ግራፍ አሽክሞ በሰላማዊ ሰልፍ ጠባ ጫሪ መፈክሮችን አሰምቷል:: በተደጋጋሚ ከድንጋይ እስከ ቦምብ የታጠቁ መንጋዎቹን በአዲስ አበባ ላይ አዝምቷል:: በጥባጭ ሰራዊት የሚመለምለውም መሬትና ገንዘብ በሕገ ወጥ ሂደት በማደል ነው:: ይህንን ለማሳካት ባለፉት ሦስት ዓመታት ሠርቷል:: በታከለ ኡማ የተጀመረው የሃብት ሽግግር በአዳነች አቤቤ ቀጥሏል:: መንግሥታዊ የመሬት ወረራ እና ንጥቂያው ተፋፍሞ አዲስ አበባን ለማጥፋት እየተሠራበት እንደሆነ የራሱ የመንግሥት ሪፖርቶች ብቻ በቂ ናቸው:: ይህም ለዘመናት ተቋርጦ የነበረው የገዳ ወረራ ዳግም የተጀመረበት ምዕራፍ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል:: የዚህ ወረራ ማጠንጠኛዋ ደግሞ አዲስ አበባ ሆናለች:: ለዚህም ነው ከተማዋ ራስ ገዝ (አድያም) መሆን አለባት የምንለው::

ገዥው ኦሕዴድም ሆነ እንደ አሸን የፈሉት ተቃዋሚ የኦሮሞ ብሔርተኛ ድርጅቶች በአዲስ አበባ ላይ ተመሳሳይ አቋም አላቸው:: ለዘመናት የተቃቡትን ደም ረስተው የሚተሻሹት ስለ አዲስ አበባ ሲያስቡ ነው:: ሁሉም ከተማዋን ለመዋጥ ይጎመጃሉ:: ለዚህም አምስቱ የኦሮሞ ድርጅቶች በኢሊሌ ሆቴል በበቀለ ገርባ አንደበት ያነበቡትን መግለጫ ማስታወሱ በቂ ነው:: ይህንን ከተማ አፍራሽ የፖለቲካ አሰላለፍ ገዥው ፓርቲም ሲቀላቀል በታከለ ኡማ ‹አዲስ አበባ የኦሮሞ የትግል ማዕከል ነች› የሚል መፈክር ታጅቦ ነው:: በቀድሞዎቹ የመዲናዋ ግዛቶች ማለትም በቡራዩ፣ በለገጣፎ እና በሱልልታ ብሎም በገላን፣ በቱሉ ዲምቱ በኮዬፈጩ እና በሌሎችም የአዲስ አበባ አካባቢዎች የተፈፀሙ አረመኔያዊ ድርጊቶች ለውጥ ተብየው ከሩቅ የሚለይባቸው ቀለሞቹ ናቸው::

የሚቀያየሩ ከንቲባዎችም የከተማዋ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባል ሳይሆኑ ሕግ እየተጣሰ እና አዲስ አፓርታይዳዊ ማሻሻያ እየተደረገ የመጡ ናቸው:: ኦህዴድ/ብልፅግና የቀድሞውን ምክትል ከንቲባ ታከለ ኡማን ወደ ሥልጣን ሲያመጣ ድርጅቱ ባስቀመጠላቸው ርዕይ አፈፃፀሙን እንዲተገብሩ ነበር:: አቶ ታከለ ተሳካላቸው ወይስ አልተሳካላቸውም ለሚለው ክርክር በዚህ ፁሁፍ ለመዳሰስ ከጊዜ አኳያ አልፈቀደልኝም:: የአዲስ አበባ ነዋሪ ላይ የተጫኑት ታከለ ኡማ አዲስ አበባን የኦህዴድ እስር ቤት ለማድረግ ብሎም የሕዝብ ስብጥር ለውጥ ለማምጣት ብዙ ጥረዋል:: በድርጅት መዋቅር የታገዘ ሥራ ተከናውኗል:: የሕዝብ ስብጥር ቅየራውን የወቅቱ የኦሮሚያ ርዕሰ መስተዳድር ለማ መገርሳ በአዲስ አበባ ውስጥ ጣልቃ ገብተው በነሲቡ አቀላጥፈውታል:: ከሶማሌ ‹ክልል› ‹ተፈናቀሉ› ተብለው የመጡ ሰባት መቶ ሺህ ኦሮሞዎች እውን ተፈናቅለው ሳይሆን በለማ ትዕዛዝ ከሰላማዊ ኑሯቸው ተነስተው የመጡ ናቸው:: ይህንን ጉዳዩ በቀጥታ ከሚመለከታቸው ሰዎች አረጋግጠናል:: እንቅስቃሴውም የገዳን ወረራ በአዲስ አበባ ለማስጀመር ያለመ ነበር:: ለዚህም ነው በአንድ አካባቢ ብቻ ራሱን የቻለ ዘመናዊ የጋራ መኖሪያ መንደር በመንግሥት ተገንብቶ የተሰጣቸው:: ዜጎች እውን ተፈናቅለው ከሆነ በዚያው በሶማሌ ‹ክልል› ቦታ የመስጠት ፍላጎት እንደነበራቸው የወቅቱ የአካባቢው ገዥዎች ጠይቀው እንደነበርም ግልፅ ነው:: ይህ አዲስ አበባን ከመውረርም በተጨማሪ የሶማሌን ማሕበረሰብ ያለወንጀሉ ደም የመቀባት አባዜ ነው:: በዚህ ከአዲስ አበባ ሕዝብ ያልተናነሰ የሶማሌም ሕዝብ ተጎጂ ነው:: ሕዝቡ አሁንም ይቅርታ ሊጠየቅና እውነታው ግልፅ ሊሆን ይገባል::

### የገዳ ወረራ

በአህዴድ በጠላትነት የተፈረጀና መጤ የተባለ ሕዝብ በየሰበቡ ተፈናቅሏል። እየተፈናቀለም ነው። በአንፃሩ የልማት ተነሽ አርሶ አደር ልጆች በሚል ሽፋን ኦሮሙማን ለመትከል እየተሠራ ይገኛል። ከልዩ ጥቅም በላይ የባለቤትነት ጥያቄው የህግ መሰረት እንዲኖረው ተረኝነት ያልተፃፈ ህግ እንዲሆን አቅም በፈቀደላቸው መጠን እየሠሩ መሆኑ እሙን ነው። በአዲስ አበባ የተፈፀሙ አሁንም እየተሰራበት የሚገኘው የድሆች መፈናቀል ቤት ፈረሳ ከተማዋን በማስዋብ ስም ቀጥሏል። የቅርስ ፈረሳውም ሌላ ዘመቻ ነው። የጋራ መኖሪያ ቤቶችን ከድሆች ነጥቆ ለወቅቱ የአህዴድ ባለስልጣናት ማደል፣ ለተመረጡ ቄሮዎች ማከፋፈል የወረራው መገለጫዎች ናቸው። የስርዓቱ ዐይን አውጣነት የሚታየውም እዚህ ላይ ነው። የባልደራስ አመራሮች እስር ቤት የተወረወርነው የዚህ ወረራ ተከላካዮች በመሆናችን ነው።

ድሃው ሕዝብ ከዕለት ጉርሱ ቆጥቦ የሠራው የጋራ መኖሪያ ቤት ለተመረጡ ግለሰቦች ሲታደል ከመቃወም የዘለለ የዳሰሳ ጥናቶች ተደርገው በርካታ መረጃዎችን በመሰብሰብ ላይ በነበርንበት ወቅት ወደ እስር ቤት ብንመጣም እውነታው ግን ሊታሰር አልቻለም። በታከለ ኡማ መንበር የተተኩት የአህዴድ ከንቲባ አዳነች አበቤ በ18/06/13 በኮተቤ ሜትሮፖሊቲያን ዩኒቨርሲቲ በባለሙያዎች ‹አስጠናሁ› ባሉት እና ስም ባወጡለት ዘረፋ 2695 የጋራ መኖሪያ ቤቶች በወቅቱ ዘራፊዎች እንደተያዙ አረጋግጠዋል። ለዚህ ንጥቂያ ተጠያቂ ያደረጉት የወቅቱ አመራሮችን ነው። ኦሕዴድ ሌባም፣ ከሳሽም፣ አጣሪም፣ ፈራጅም ራሱ የሆነበት ገጠመኝ።

አቶ ታከለ ኡማ ከሓላፊነታቸው ከተነሱ በኋላ ለሪፖርተር ጋዜጣ በሰጡት ቃለ መጠይቅ 21 ሺህ የጋራ መኖሪያ ቤቶችን ለኦሮሞ ተወላጆች ማደላቸውን በኩራት ተናግረዋል። እቅዳቸው ለ65 ሺህ የኦሮሞዎች ገበሬዎች ማደል እንደነበርም ጨምረዋል። ታከለ እና የኦሕዴድ ጓዶቻቸው ራሳቸው ባመኑት መሠረት ቢያንስ በዚህ ወንጀል መጠየቅ ነበረባቸው። አሁንም ሊጠየቁ ይገባል። ፍርዱን ለታሪክ መተው ይሻላል። በአዳነች አበቤ ሪፖርት መሠረት እንኳን ከጋራ መኖሪያ ቤቶች መካከል 5 ሺህ ያህሉ ለመንግሥት አመራሮች ብቻ ነው የተሰጡት። ይህ መንግሥታዊ ውንብድና ነው። ለየትኞቹ አመራሮች እንደተሰጠም ስም ተጠቅሶ መብራራት አለበት። ደላሎቹ እነማን እንደሆኑም ሪፖርቱ ምላሽ ሊሰጥ ይገባል። ይህ ብቻ ሳይሆን ቤቶቹን ሊመልሱ እና በሂደቱ ተሳታፊ የሆኑ ሁሉ በሕግ ሊጠየቁ ይገባል።

በአዲስ አበባ የሚደረገው የአህዴድ መቆሚያ ያጣ ተረኝነት ድርጅቱ ከምርጫ ይልቅ ለውጊያ የተዘጋጀ በሚመስልበት በአሁኑ ጊዜ ፖለቲካው እንዳይረጋጋ አድርጎታል። ባለመረጋጋቱ ውስጥ ደግሞ የገዳ መንግሥታዊ ወረራ እየተስፋፋ ነው። በአዲስ አበባ እና በቤንሻንጉል ጉምዝ እየተሰጠ ያለው የኦሮምኛ ትምህርትም የወረራው መገለጫ ተደርጎ ቢወሰድ ስህተት አይሆንም። ደቡብ ኢትዮጵያን የመተልተሉ እንቅስቃሴ ለዚህ ማስፈፀሚያ ስልት የተቀየሰ ነው።

### መጪው ምርጫና አዲስ አበባ

የአዲስ አበባ ለዓመታት የተወሳሰቡ ችግሮችና አስተዳድራዊ ጥያቄዎቿ በመጭው ምርጫ መልስ ያገኛሉ ብየ አስባለሁ። ሕዝቡ በፌዴሬሽን ምክር ቤት የፖለቲካዊ ውክልና ጥያቄ አለው። የኑሮ ውድነት ሰቀቀን ሆኖበታል። የመኖሪያ ቤት ችግሮች፣ የሥራ አጥነት ጣጣ፣ የትራንስፖርት ስቃይ በጥቂቱ የሚጠቀሱት ችግሮቹ ናቸው። አሁንም ችግሮቹ አድማስ አልፈው የሕልውና ጉዳይ ሆነዋል። ለዓመታት ከኖሩበት ቤታቸው ውጡ የሚባሉት፣ እላያቸው ላይ ቤታቸው የሚፈርሰው፣ ኮሽ ባለ ቁጥር ቆንጨራ የሚቃጣባቸው እና ከድንጋይ እስከ ቦምብ የሚወረወርባቸው አዲስ አበቤዎች ቀላል አይደሉም። ኗሪው የእኩል ተጠቃሚነት መብትም የለውም። ኦሮሞ ያልሆነ ሁሉ ሁለተኛ ዜጋ ሲሆን ዐማራ ደግሞ በግልፅ በጠላትነት ተፈርጆ እየተሳደደ ይገኛል።

አዲስ አበባ ለዚህ መልስ የሚሰጥ አስተዳድር መሰየም ይኖርባታል። በቅርቡ ከ51 ሺህ በላይ ለጋራ መኖሪያ ቤት ዕጣ የወጣላቸው እድለኞች በህጋዊ መንገድ ተመዝግበው ከእለት ጉርስ ቆጥበው የደረሰው መኖሪያ ቤት አይናቸው እያየ ለአህዴድ ተረኞች ሲሳይ ተደርጓል። መጭው ምርጫ ለአዲስ አበባ ወሳኝ የሚሆነውም ለዚህ ነው። ሂደትና ውጤቱንም በአይነ ቁራኛ መከታተል ያስፈልጋል።

የአዲስ አበባ ነዋሪዎች በገዛ ሀገራቸው ተገፍተው ሜዳ ላይ ወድቀዋል። የቤት ተስፋቸው የቄሮ ውርስ ሆኗል። በአዲስ አበባ አስሩም ክፍለ ከተሞች፣ በ116 ወረዳዎችና በ817 ቀጠናዎች ባዶ መሬት በጠራራ ፀሐይ ለወራሪ ቡድን በማደል በአንድ ጀንበር ቱጃር ሀብታም ሲፈጠር እያየን ነው። ከፊሎቹም የመሬት ንግዱን አጧጡፈውታል። አዲስ አበቤ እስከ ሃያ ዓመታት የኖረበት ቤት እላዩ ላይ ሲፈርስበት ‹መጤ› እና ‹ሰፋሪ› የሚል መለዮ እየተለጠፈበትም ጭምር ነው። ይህ ችግር ተደማምሮ ነው እኛም ወደ ፓርቲ ትግል የገባነው።

እነዚህና መሰል ነገሮች እየተስፋፉ በመምጣታቸው በህዝብ እሮሮ ባልደራስ ለእውነተኛ ዴሞክራሲ ፓርቲ (ባልደራስ) ተመስርቷል። ፓርቲያችን የልዩ ጥቅም ፍላጎት ችግሮችን በመንቀስ ስርዓቱን ለማሳየት በስፋት ተንቀሳቅሷል። ለመፍትሄው ህዝቡ እንዲዘጋጅ ሃቀኛ የፖለቲካ ዝግጅት በመፍጠር ብዙ ሰርቷል። በርካታ የታሪክ አሻራዎችን አስቀምጧል። መሠረታዊ የድርጅት ግንባታን ከወቅቱ ፖለቲካዊ አክቲቭዝም ጋር በማጣጣም ህዝብን ለማንቃት ተችሏል። ይህ ተግባር በኢትዮጵያ የፓርቲ ፖለቲካ ታሪክ ውስጥ ያልተለመደ ነው። የሕዝቡን ችግሮች አብረን በመቅመሳችንም ባልደራስ በአጭር ጊዜ ውስጥ ወደ ህዝብ ልብ እንዲገባ አስችሎታል።

የአርቲስት ሀጫሉ ሁንዴሳ ግድያን አስመልክቶ ታከለ ኡማ አዲስ አበባን ዙሪያ አስከብበው ባስማሩት ቄሮ የጥፋት ተልዕኮ ከሽመልስ አብዲሳ ጋር ማስፈፀማቸው የአደባባይ ሚስጥር ሆኖ አልፏል። በግለሰቡ ጥያቄ ሳይኖራቸው በተለዋጭ ሹመት ሚንስትር አድገው ለሌላ ዝርፊያ አመቻችተዋቸዋል። ወደ ማዕድን ሚንስትርነት በተዘዋወሩ አፍታ የከፋት ጡንቻቸውን የሚደርቁ የወርቅ ኩባንያዎች ላይ አሳርፈዋል።

ታከለ ከከንቲባነት ከተነሱ በኋላ በምክትላቸው የመጡት የአህዴድ/ብልፅግና ቀዳማዊ እመቤት አዳነች አበቤ የድርጅታቸውን እኩይ ርዕይ እያስቀጠሉ እንደሆነ አያጠራጥርም።

አህዴድ ተነስቶ አህዴድ መጣ። አዲስ አበባ ከታከለ ኡማ ወደ አዳነች አበቤ ተሸጋገረች። በአሁኑ ወቅት በመዲናዋ እየተባባሰ ያለው የኦሮሙማ መስፋፋትና አስደንጋጭ ወረራ ቀደም ሲል የተያዘ የአህዴድ ዘመቻ ተጠናክሮ እንደቀጠለ እንግሊዝ ኢምባሲ አካባቢ ያለው ሁኔታ ጥሩ ማሳያ ነው።

በመሆኑም በሀገራችንም ሆነ በከተማችን አዲስ አበባ ትውልዱን የመታደግ ሓላፊነት ከፊታችን እየመጣ እንደሆነ ይሰማኛል። የአዲስ አበባ ችግር የሚፈታው በማዘጋጃ ቤት ሳይሆን በ4 ኪሎ እንደሆነ ባምንም የማዘጋጃ ቤትን 138 ወንበር መቆጣጠር የፕሮቶኮል ጉዳይ ሳይሆን የህልውና ጥያቄ መፍቻ ነው።

የነዋሪው ሰላምና ደህንነት ማጠበቂያ ነው። የዚህ ትውልድ አድዋ ነው። አዲሱ ታሪክ ብረት ማንገብ ሳይሆን የምስርጫ ስራዊት መፍጠር ነው። ህልውናውን በካርዱ ድምፅ በአደባባይ አብዮት ማስጠበቅ ምርጫችን ሳይሆን ግዴታችን ጭምር ተደርጓል። ይህ ምርጫ በተለይ ለአዲስ አበቤ ነፃነቱን የሚያውጅበት ሕዝበ ውሳኔ ነው ማለት ይቻላል። ምርጫ የተበታተነ ድምጽ ይዞ እንዳይመጣ ፖለቲካዊ ቅንጅቶች ተጠናክረው ሊቀጥሉ ይገባል። ከዚህ አንፃር የአማራ ብሔራዊ ንቅናቄ ፣ ባልደራስ ለእውነተኛ ዴሞክራሲ፣ የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅትና የኢትዮጵያ ብሔራዊ አንድነት ፓርቲ የጀመርነው ጥምረት ይበል የሚያሰኝ ነው። ሌሎች ፓርቲዎችም ጥምረቱን ሊቀላቀሉ ይገባል።

አዲስ የኃይል አሰላለፍ ያስፈልጋል። በተመረጡ ሀሳቦች ላይ አብሮ መቀናጀት የህልውና ጥያቄው ቁልፍ መሳሪያ ነው። መንግሥታዊውን የገዳ ወረራ መመከቻ መንገዱም አብሮነት ነው።



# የአዲስ አበባ ራስ ገዝነት

## (ክፍል ፩)

## ያለፉት 50 ዓመታት የአዲስ አበባ የራስ ገዝነት አስተዳደር ልምድ

በደርግ ዘመን መጀመሪያ ማለትም በ1968 ዓ.ም የአዲስ አበባ ከተማን የከተማ ቦታ ኪራይ እና የከተማ ቤት ግብር አዋጅ ለመደንገግ የደርግ መንግሥት ባወጣው አዋጅ ቁጥር 80/1968 ጋር አባሪ ተደርጎ የቀረበው የከተማዋ ካርታ ከተማዋ የትኞችን በዙሪያዋ የሚገኙ ቦታዎች እንደምታካትትና ስፋቷም 122,000 ሄክታር እንደነበር ተመልክቷል:: በካርታው ውስጥ አሁን "የፊንፊኔ ዙሪያ ልዩ ዞን" በሚል የተካተቱ ቦታዎች በአዲስ አበባ የቀድሞ ይዞታ ስር እንደነበሩ በግልጽ ተመልክቷል:: /ካርታው ከነአዋጁ በአባሪነት ቀርቧል/

በደርግ ዘመን በ1981 ዓ.ም የራስ ገዝ አካባቢዎችን፣ የአስተዳደር አካባቢዎችንና የአውራጃዎችን ለመወሰን አዋጅ ቁጥር 26/1981 በታወጀበት ጊዜ አዋጁ አዲስ አበባን በ13 የከተማ ክ/ከተሞች፣ በ20 የገጠር አውራጃዎች ከፍሏቸው ነበር:: ክ/ከተማዎቹ አራዳ፣ ተክለሃይማኖት፣ አዲስ ከተማ፣ ኮልፌ፣ ጉለሌ፣ ቀጨኔ፣ እንጦጦ፣ የካ፣ ቦሌ፣ ንፋስ ስልክ፣ ቂርቆስ፣ ልደታ፣ ኮተቤ ሲሆኑ የገጠር የአዲስ አበባ አውራጃዎች ደግሞ በሰቃ፣ በረህ፣ ዓለምገና፣ ወልመራ፣ ሱልልታና አቃቂ ነበሩ:: እነዚህ የአዲስ አበባ የገጠር አውራጃዎች በሥራቸው 25 ወረዳዎች ነበሯቸው:: /ዝርዝሩ ከዚህ መግለጫ ጋር በአባሪነት ተያይዟል/::

ከላይ እንደተጠቀሰው ከንጉሡ ዘመን ጀምሮ እስከ ደርግ ዘመን መጨረሻ ጊዜ ድረስ የአዲስ አበባ ስፋት 122,000 ሄክታር እንደነበር ልብ ይሏል:: አዲስ አበባ በውሃና እህል አቅርቦት ረገድ ራሷን የቻለች ከተማ ነበረች:: የገፈርሳ ውሃና በአቃቂ ዙሪያ የሚገኘው ከፍተኛ የከርሰ ምድር ውሃ በአዲስ አበባ ከተማ ይዞታ ስር ነበር:: በአዲስ አበባ ይዞታ ስር በከተማዋ ዙሪያ የነበሩ በርካታ የቀበሌ የገበሬ ማህበራት ከአራቱም የኢትዮጵያ ማዕዘናት ማለትም የአማራ፣ የኦሮሞ፣ የጉራጌ እና ሌሎች የደቡብ ብሔረሰቦች ከኤርትራ ሃማሴን ሳይቀር የመጡ ሰዎች መሬት ከባለ መሬት እየተከራዩ የተለያዩ የጓሮ አትክልት እና የእህል ሰብል የሚያመርቱ ገበሬዎች የሚኖሩባቸው አካባቢዎች ነበሩ:: በአጭሩ አዲስ አበባ ከመላ ኢትዮጵያ ኢትዮጵያውያን መጥተው ኑሯቸውን የሚመሰርቱበት፣ በገበሩት ግብር ያለሟት፣ የክፍለ ሃገር ኑሮ እድገታቸውን/ መሻሻላቸውን እንደሚገታ ሲገምቱ ወይም በተለያዩ ችግር ምክንያት ሲፈናቀሉ የሚመጡባትና የሚጠለሉባት ከተማ ሆና የኖረች ናት::

አዲስ አበባ አሁን የሚኖርባት ነዋሪ አባቶችና ቅድመ አያቶች ከየቦታው እየመጣ መኖሪያ እና መጠለያ ያደረጋት ኢትዮጵያዊ ሁሉ ነው:: እስከ ህወሓት ዘመን ድረስ ኦሮሚያ የሚባል ግዛት / ክልል/ አልነበረም:: በኋላ የመጣ እንጂ ቀደም ሲል

በቦታው የነበረ ከኋለኛው ሊወስድ አይችልም:: ሊወስድ የሚችለው በኋላ የመጣው ነው:: ባለፉት 30 ዓመታት ወያኔ ከአማራው ክልል መሬት ነጥቆ ወደ ትግራይ እንደከለለው ሁሉ ህወሓት እና ኦነግ እና ኦህዴድን ለማስደሰት ሲል ቀደም ሲል በኢትዮጵያ ታሪክ የማይታወቅ ኦሮሚያ የተሰኘ ክልል ፈጠረ:: ይሄ አይነት አከላለል በኢትዮጵያ የጥንትም ሆነ የመካከለኛው ዘመን የኢትዮጵያ ታሪክ የሚታወቅ አይደለም:: ይሄ አዲስ ክልል ነው:: ኢህአዴግ ስልጣን ከያዘ ከ1983ዓ.ም ጀምሮ የሽግግር ወቅት በመባል የሚታወቀው ከሰኔ 1983 ዓ.ም - ነሐሴ 1987 ዓ.ም በነበሩት አራት ዓመታት ውስጥ አዲስ አበባ ክልል 14 ተብላ እንደ ሌሎች የህወሐት/ኢህአዴግ ክልሎች ራሷን የቻለች ክልል እንደነበረች የሚታወቅ ነው:: በህወሓት ኢህአዴግ ዘመን በተለይ ከ1997 ዓ.ም የምርጫ ሽንፈት በኋላ የአዲስ አበባ ይዞታ በየጊዜው እየጠበበ እንዲሄድ ተደርጎ ጽንፈኛ ብሔረተኞች የራሳችን ነው ወደሚሉት የኦሮሚያ ክልል እንዲካለል በማድረግ የአዲስ አበባ ይዞታ ቀደም ሲል ከነበረው እንዲቀንስ የከተማው አስተዳደርም ከከተማው ነዋሪ እጅ ወጥቶ በሞግዚት አስተዳደር ስር እንዲገባ ተደረገ::

በህወሓት/ኢህአዴግ የአገዛዝ ዘመንም ቢሆን በወያኔ/ኦነግ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 49፣ ንዑስ አንቀጽ1 መሠረት አዲስ አበባ የፌዴራል መንግሥቱ ዋና ከተማ መሆኗ ተመልክቷል:: የወያኔ/ኦነግ ህገ መንግሥትም ቢሆን በአንቀጽ 49 ንዑስ አንቀጽ 2 የአዲስ አበባ ነዋሪ ራሱን በራሱ የማስተዳደር መብት ሰጥቶታል:: ከ1987 ዓ.ም እስከ 2011 ዓ.ም ድረስ የአዲስ አበባ ከተማ በየጊዜው ሲሻሻሉ የቆዩ ቻርተሮችም ቢሆኑ የከተማዋ ነዋሪ ራሱን በራሱ የማስተዳደር ሙሉ መብት እንዳለው አስረግጠ አስፍሯል:: የኢፌዲሪ ህገ መንግሥት የአዲስ አበባ ነዋሪ ራሱን በራሱ ማስተደዳር ይችላል የሚል ድንጋጌ ቢኖረውም ለይስሙላ ብቻ እንደላንቲካነት ሲያገለግል በቆየባቸው ባለፉት ሃያ አምስት ዓመታት የአዲስ አበባ ሕዝብ የሃገሪቱ የፌዴራል ስርአት እንደሚደነግገው፣ ነዋሪው ራሱ በመረጣቸው ሰዎች አስተዳድሮ አያውቅም:: ባለፉት 30 ዓመታት ሌሎች ክልሎች ለይስሙላም ቢሆን ከየክልላቸው በተመረጡ ሰዎች ሲመሩ አዲስ አበባና ድሬደዋ ይህ መብት እስካሁን ድረስ ተነፍጓቸው ከሌሎች ክልሎች በሚመጡ ሰዎች የሞግዚት አስተዳደር ስር እንዲወድቁ ተደርገዋል::

ከላይ በቀረቡ ተጨባጭ መረጃዎች እንደተመለከተው አዲስ አበባ በዙሪያዋ ይኖሩ የነበሩ ገበሬዎች በከተማ ቀመስ የገበሬ ማህበራት ስር የታቀፉ ነበሩ:: ወደ በኋላ በአዲስ አበባ ማስተር ፕላን ምክንያት ተፈናቀሉ የተባሉት ገበሬዎች ይኖሩበት የነበረው የአዲስ አበባ ዙሪያ አካባቢ ከአዲስ አበባ ተቆርጦ "የፊንፊኔ ልዩ ዞን" በሚል ከአዲስ አበባ በተወሰደ መሬት ላይ የሚኖሩ ገበሬዎች ነበሩ:: እውነተኛው ክንውን የአዲስ አበባ ማስተር ፕላን የተቀየሰው ከአዲስ አበባ በተቀማው የከተማዋ መሬት ላይ እንጂ ከኦሮሚያ ክልል በተወሰደ መሬት ላይ አይደለም::

ከ1997 ዓ.ም የህወሓት ሽንፈት በኋላ አቶ መለስ ዜናዊ ኦህዴድን ከናዝሬት/አዳማ ወደ አዲስ አበባ እንዲመለስ አደረገ:: የአዲስ አበባ ይዞታ ቀድሞ ከነበረበት ወደ 54,000 ሄክታር እንዲጠብ ተደረገ:: ከ1997 ዓ.ም በኋላ ህወሓት በአዲስ አበባ ዙሪያ ብዙ የጋራ መኖሪያ ቤቶች መሥራት ሲጀምር ከተማዋ እየተለጠጠች ከኦሮሚያ ክልል ጋር "የድንበር አለመግባባት" ችግር ተፈጠረ:: የድንበር አለመግባባቱ የተፈጠረው የአዲስ አበባ የቀድሞ ይዞታ የነበረውን ህወሓት ከአዲስ አበባ ነጥቆ " የፊንፊኔ ልዩ ዞን" በሚል ወደ ኦሮሚያ እንዲካለል በማድረጉ ነው:: የተፈጠረውን ችግር ለመፍታት በ2009 ዓ.ም በዶ/ር አብይ የሚመራ ኮሚቴ የአዲስ አበባን ከተማ ከኦሮሚያ እና ከአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት የተውጣጡ ባለሙያዎች እንዲያጠኑት ተደረገ:: በተደረገው ጥናት በወቅቱ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ስር ያለው ይዞታ 54,000 ሄክታር እንደሆነ ቢገለጽም በተጨባጭ ግን የጥናቱ ውጤት ያሳየው በአዲስ አበባ አስተዳደር ስር ሆኖ የተገኘው ወደ 51,355 ሄክታር ቀንሶ ነበር:: ይህም የሆነው ምንም አይነት አዋጅ ሳይደነገግ በውስጥ ለውስጥ አሠራር ነው:: በአዲስ አበባ ዙሪያና በአዲስ አበባ ዙሪያ የነበሩት-እነ ሰበታ፣ ሰንዳፋ፣በኮተቤ አንቆርጫ፣ የካ አባዶ፣ የካ ጣፎ፣ ቦሌ ኮተቤ፣ ሱልልታ፣ (በበሰቃ ውስጥ አቃቂና አቃቂ ከተማ፣ ሰርቲ፣ ከዩ፣ ገላን ጎራ፣ ቂሊንጦ፣ ፈጬ፣ ቀርሳ፣ ቱሉ ሜጫ) በረህ፣ ዓለም ገና፣ ወልመራ፣ ወዘተ...ወደ ኦሮሚያ ክልል እንዲጠቃለሉ መደረጉ ይታወሳል:: ከ 2009 ዓ.ም ጀምሮ የአዲስ አበባን ማስተር ፕላን ጥናት በተመለከተ የተቀሰቀሰውን ተቃውሞ ምክንያት በማድረግ በኦህዴድ ውስጥ የተነሳው ውዝግብ በእነ ድሪባ ኩማና ኩማ ደመቅሳ በኩል አዲስ አበባ በሕወሓት/ኢህአዴግ ዘመን በተለይም ከ1997ቱ ምርጫ በኋላ ሕወሓትና ኦህዴድ ተስማምተው በወሰኑላት የ54,000 ሄክታር ይዞታ መጠን ላይ መሆን አለበት ሲሉ በዶ/ር አብይና በአቶ ለማ በኩል ደግሞ የአዲስ አበባ ከተማ ይዞታ ወደ 43,000 ሄክታር ዝቅ ማለት አለበት የሚል አቋም ተያዘ:: ይህ ውዝግብ መቋጫ ሳያገኝ በመጋቢት 2010 ዓ.ም ህወሓት/ኢህአዴግ ቦታውን ለኦህዴድ ለቀቀ:: ኦህዴድ ውስጥ አሸናፊ ሁኖ የወጣው የጠቅላይ ሚ/ር አብይ አመራር ቀደም ሲል ባቀረበው ሃሳብ በመጽናት ከአዲስ አበባ 30 ወረዳዎች ተቀንሰው ወደ ኦሮሚያ እንዲካለሉ ይፈልጋል:: ይህም ወደ ዝርዝር ሲተረጎም ከየካ ክ/ከተማ 6 ወረዳዎች፣ ከንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከተማ 1 ወረዳ፣ ከአቃቂ ክ/ከተማ 7 ወረዳዎች፣ ከጉለሌ ክ/ከተማ 5 ወረዳዎች ፣ ከቦሌ ክ/ከተማ 2 ወረዳዎች፣ ከኮልፌ ቀራኒዮ ክ/ከተማ 9 ወረዳዎች ማለት ነው:: አሁን በወ/ሮ አዳነች ምክትል ከንቲባነት ዘመን ይህን ቀደም ሲል በዶ/ር ዐብይ አህመድ ሲመራ የነበረው ኮሚቴ ሲያራምድ የነበረውን 30 ወረዳዎች፣ ከአዲስ አበባ ቀንሶ ወደ ኦሮሚያ የማካለል ፍላጎት አዲስ አበባ በኦሮሚያ ክልል ሙሉ ጥገኝነት ስር እንድትወድቅ ለማድረግ ያለመ ነው:: ይህ አካሄድ አዲስ አበባን በኢኮኖሚ ረገድ እንደቀድሞዋ ራሷን እንዳትችል እና ከኦሮሚያ ክልል በምታገኘው ልዩ ጥቅም ተንበርካኪ እንድትሆን የሚያደርግ አካሄድ ነው::

በኦሮሞ ብልጽግና ብቻ ሳይሆን በሁሉም የኦሮሞ የፖለቲካ ድርጅቶች መካከል የተደረሰው ስምምነት አዲስ አበባ በህገ መንግሥቱ የተሰጣትን የራስ በራስ አስተዳደር በመንጠቅ ልዩ ጥቅም የሚለውን ግልጽ ያልነበረ እስካሁንም ዝርዝር ሕግ ያልወጣለት የሕገ-መንግሥት አንቀጽ ሰርዞ፣ ሙሉ ለሙሉ በኦሮሚያ ክልል ውስጥ በባለቤትነት እንድትካተት ማድረግ ነው:: በፖለቲካውም ሆነ በኢኮኖሚው ረገድ በዶ/ር ዐብይ መንግሥት እየተከናወነ ያለው ተግባር በጥሞና ሲታይ ወደዚህ ግብ የሚያመራ እንደሆነ በግልጽ ይታያል:: ኦህዴድ/ብልጽግና እና በኦሮሚያ ክልላዊ መስተዳድር በመደገፍ የኦሮሞ ጽንፈኛ ብሄርተኞች በአዲስ አበባ ላይ ያነሱት የባለቤትነት ጥያቄ ከታሪክ የሚቀዳ ነው የሚል ከታሪክም፣ ከሕግም፣ ከአስተዳደራዊ አወቃቀር ልምድም አንፃር ያፈነገጠ አሠራር ነው:: ይህ ድርጊት ደግሞ ታሪክን በተንሸዋረረ መነጽር ከመመልከት የመነጨ አባዜ እንጂ የነሱ የባለቤትነት ጥያቄ ከተጨባጭ የታሪክ ማስረጃዎች አንፃር ውሃ የሚቋጥር ሆኖ አይደለም::

በተጨባጭ ማስረጃ የሚደገፈው ታሪክ መሃል ኢትዮጵያ በኦሮሞ ጎሳዎች ከመወረሩ ከ16ኛው ክፍለ ዘመን በፊት አዲስ አበባና አካባቢዋ ብቻ ሳትሆን መላ ሸዋ የአማራ፣ የጉራጌ፣ በሂደት ወደ አማራነት የተለወጡ የሃርላ እና የጋፋት ሕዝቦች አጽመ ርስት የነበረ መሆኑ ነው:: ጽንፈኛ የኦሮሞ ብሄርተኞች ይዞታ ከታሪክ ይቀዳል በሚል አካሄዳቸው "ከአጼ ምንሊክ ጀምሮ ያለው የኢትዮጵያ ታሪክ ኦሮሞ በነፍጠኛው ስርዓት በቅኝ የተገዛበት ታሪክ ነው፤ ነፍጠኛን በሰበረን ቦታ ሰብረነዋል፤ አሁን ኦሮሞ ስልጣን ከያዘ አዲስ አበባን በባለቤትነት እንጠቀልላለን" በሚል የተሳሳተ የታሪክ ትርክታቸው ከፀኑ እነሱ ሙልጭ/በዜሮ/ የሚወጡበትን አካሄድ እየተከተሉ መሆኑን ሊገነዘቡት ይገባል:: የኦሮሙማ አቀንቃኝ ጽንፈኛ ብሔረተኞች ሁሉም የኛ ነው ከሚል ለከት የለሽ አካሄዳቸው ታቅበው፣ ኢትዮጵያም ሆነች አዲስ አበባ የሁላችንም ኢትዮጵያውያን የጋራ ይዞታ መሆናቸውን ሊቀበሉ ይገባል:: ከዚህ

ውጭ ያለው አካሄድ የርስ በርስ ጦርነት ከመጋበዝ እና በሁሉም ላይ ጥፋት ከማስከተል ውጭ ማንም ወገን ለብቻው የሚያተርፍበት ሁኔታ ሊኖር እንደማይችል በውል ሊያስተውሉት ይገባል።

እንደ ባልደራስ ለእውነተኛ ዲሞክራሲ ፓርቲ እምነት የአዲስ አበባ ጉዳይ ወደ ቀድሞው ይዞታዋ መመለስ ይኖርባታል። ይህም ማለት የይዞታ ዳር ድንበርን በተመለከተ አዲስ አበባ በንጉሱ ጊዜ እና በደርግም እስከ 1987 ዓ.ም ድረስ ወደ ነበረው የ122,000 ሄክታር ይዞታዋ መመለስ ይኖርባታል። የራስ ገዝ አስተዳደር ጉዳይንም በተመለከተ በንጉሡ ዘመን፣ በደርግ ዘመን እንዲሁም በህወሓት/ኢህአዴግ የሽግግር ወቅት ዘመን ወደ ነበረችበት የራስ ገዝ አልያም/ክልል የአስተዳደር ደረጃ ልትመለስ ይገባል። በ1987 ዓ.ም የፀደቀውና እስካሁን ያልተሻረው የኢፌድሪ ህገ መንግሥት አዲስ አበባ ከሞግዚት አስተዳደር ስር ወጥቶ ነዋሪው በነፃነት በመረጣቸው ወኪሎቹ ሊተዳደር ሲገባ፣ በአንቀጽ 49 ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ተጠሪነቱ ለፌዴራል መንግሥቱ እንዲሆን ተደነገገ። የአዲስ አበባ የራስ ገዝነት ጥያቄ በታሪክም ሆነ በሕግ የተደገፈ እድሜው ከ30 ዓመት በላይ የሆነ ማንም ኢትዮጵያዊ የሚያውቀው እና የሚያስታውሰው ስለሆነ ሁሉም የኢትዮጵያ ብሔረሰቦች እና የፖለቲካ ኃይሎች ሊደግፉት ይገባል። ስለዚህ በዜግነት ዙሪያም ሆነ በክልል ደረጃ የተደራጁ የፖለቲካ ድርጅቶች አዲስ አበባ ኢትዮጵያ ውስጥ ባሉ ከሰማንያ በላይ ከሆኑ ብሔረሰቦች በተውጣጡ ሕዝቦች ላብ የተገነባች መሆኗን በመረዳት እና እውነተኛ ታሪካዊ ዳራውን በማጤን እራሷን እንድታስተዳድር ሙሉ ተግባራዊ ድጋፋቸውን እንዲያበረክቱ ታሪካዊ፣ሕጋዊ እንዲሁም ሞራላዊ ኃላፊነት ወድቆባቸዋል። ስለሆነም አዲስ አበባ የመላ ኢትዮጵያ ብሔረሰቦች መገናኛ እና ማዕከል ሆና መቀጠል አለባት የሚል አቋም ያላቸው የፖለቲካ ኃይሎች/ድርጅቶች የተነሳውን የአዲስ አበባ ከተማ የተሟላ የራስ ገዝነት ጥያቄ በመደገፍ በጋራ ሊንቀሳቀሱ ይገባል ብሎ ስለሚያምን ባልደራስ ለእውነተኛ ዲሞክራሲ ፓርቲ ጥሪውን በአክብሮት ያቀርባል።

### አዲስ አበባ ራሷን እንድትችል ቢደረግ የሚገኘው የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና የማህበራዊ ጥቅም ምንድን ነው?

### ሀ. በፖለቲካ ረገድ

ሀ.1. እንደሚታወቀው ባለፉት ሰላሳ ዓመታት የኢትዮጵያዊነት ስሜት እና የዜግነት ፖለቲካ እንዲደበዝዝ ብሎም የጎሳ ፖለቲካ የበላይነቱን እንዲይዝ ሊደረግ የቻለው የኢትዮጵያዊነት የጠነከረ ስሜት እና የዜግነት ፖለቲካ ብቸኛ መናኸሪያ ሁኖ የተገኘችውን አዲስ አበባን የየስሙላ ፌዴራሊዝም በታወጀበት የኢፌድሪ ህገ መንግሥት እንኳ የተሰጣትን የራስ ገዝነት መብት በመከልከልና በሞግዚት አስተዳደር ውስጥ እንድትወድቅ በማድረግ ነው።

ሀ.2. ቀን ተለሊት አላማቸውን ለማሳካት እየሰሩ ያሉት ጽንፈኛ የኦሮሞ ብሔረተኞች በማታለልም ሆነ በማሳመን አዲስ አበባ እውነተኛ የራስ ገዝ መብት እንዳትጎናፀፍ የማድረግ ጥረታቸው ካልተገታ የኢትዮጵያ አንድነት አደጋ ላይ የሚወድቅ ከመሆኑም በላይ የዜግነት ፖለቲካ የመጨረሻው ድንበር (The Last Frontier) ይጣሳል።

ሀ.3. ኢትዮጵያ ከጎሳ ፖለቲካ ሳትላቀቅ በኢትዮጵያ ወደ ዲሞክራሲ የሚደረገው ሽግግር በምንም ተአምር ግቡን ሊመታ አይችልም። አዲስ አበባ ደግሞ የጎሳ ፖለቲካን የሚጠየፍ እና የኢትዮጵያዊነት ስሜትን የተላበሰ፣ በተጨባጭ የመላ ኢትዮጵያ ብሄረተሰቦች መናኸሪያና በ1997ቱ ምርጫ ላይ እንደታየው የዜግነት ፖለቲካ አራማጅ፣ የዘመነና ለዘመናዊ የፖለቲካ አስተሳሰብ የተጋለጠ እና የቀረበ፣ የውህድ ኢትዮጵያዊነት ብቸኛ መገለጫ ናት። ኢትዮጵያ ወደ ዲሞክራሲ የምታደርገው ሽግግር ሊጀመርና ወደ መላ ኢትዮጵያ ሊስፋፋ የሚችለው የፌዴራሊዝም ሆነ የዲሞክራሲ ውህድ አስተሳሰብ የተዋሃዳትን የአዲስ አበባ ከተማ የራስ ገዝነት መብት በተጨባጭ ማረጋገጥ ሲቻል ነው።

### ለ/ በኢኮኖሚ ረገድ

ለ.1. አዲስ አበባ ከኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ከ40-50 በመቶውን የሚሆነውን ሃብት የምታመነጭ የሃገሪቱ የኢኮኖሚ ዋነኛ ሞተር የሆነች ከተማ እንደመሆኗ፣ ጽንፈኛ ብሔረተኞች ይህንን ሀብት በመቀራመት የፖለቲካ ፍላጎታቸውን ከግብ ለማድረስ በመሳሪያነት ሲጠቀሙበት ቆይተዋል፣ አሁንም እየተጠቀሙበት እንደሆነ ይስተዋላል። በቅርቡ የኦሮሞ ብልጽግና ፓርቲ የመደባቸው ም/ከንቲባ ወ/ሮ አዳነች አበቤ ከአዲስ አበባ በጀት ላይ 680 .000 /ስድስት መቶ ሰማንያ ሚሊዮን ብር / ቀንሰው ለፊንፊኔ ልዩ ዞን ተማሪዎች የደንብ ልብስ መግዣና ለምግብ አቅርቦት ማዋላቸው ለዚህ አባባል አይነተኛ ማረጋገጫ ነው።

### ለ.2. ኢትዮጵያ የምትመራበት የዘውግ ፖለቲካ የተቋማዊ ሙስና (Institutional Corruption) ምንጭ ነው።

በኢትዮጵያ እንደ ነቀርሳ እንዲስፋፋ እየተደረገ

ያለው ሙስና የአዲስ አበባ ፖለቲካን በሞግዚት የዘውግ አስተዳደር ውስጥ እንድትወድቅ በማድረግ ነው። እንደሚታወቀው የአዲስ አበባ የመሬት ዋጋ ከቶክዮ እና ከኒዮርክ ከተሞች የሚስተካከል ነው። በኢትዮጵያ ደግሞ የዘውግ ፖለቲካ በርካታ የፖለቲካ ደጋፊዎችን ለማፍራት የቻለው የአዲስ አበባን መሬት በመቸብቸብና ሲፈልግም ለደጋፊዎቹ ከሕግና መመሪያ ውጭ በነፃ በማደል ነው። አዲስ አበባ እውነተኛ የራስ ገዝ መብቷን እንድትጎናፀፍ ማብቃት ማለት በአንድ በኩል የዘውግ ፖለቲካን የኢኮኖሚ አቅም ማዳከም ሲሆን፣ በሌላ በኩል ደግሞ የነፃ ገበያ አይነተኛ መገለጫ የሆነው የኢኮኖሚ ምህዳሩ ሁሉም ኢትዮጵያዊ በኩል የሚወዳደርበትን ሁኔታ የሚያመቻች ይሆናል። የዚህ ድምር ውጤት ደግሞ ዜጎች ፍትሃዊ የኢኮኖሚ ተጠቃሚነታቸውን እንዲያጎለብቱ ያስችላቸዋል። የአገሪቱን እድገት ሊሳለጥ የሚችለው ፖለቲካው በኢኮኖሚው ውስጥ ጣልቃ መግባቱን ሲያቆም ነው።

ለ.3. ኢትዮጵያ ውስጥ ቀደም ሲል ያልነበረ ከህወሓት/ኢህአዴግ ሥልጣን መያዝ ጋር በአዲስ የተስፋፋው ተቋማዊ ሙስና በኢኮኖሚ ተዋንያኖች መካከል የፈጠረው በሥራ ሳይሆን በአቋራጭ በሙስና የመክበር ስሜትን ፈጥሯል። በዚህም የተበላሸ አዝማሚያ ምክንያት የገበያ ሕጉ እንዲዛባና ገበያው በእውነተኛ አልሚዎች ሳይሆን በአቋራጭ በልፃጊዎች እንዲሞላ አድርጎታል። የአዲስ አበባ ራስ ገዝነት ይህንን የተበላሸ አካሄድ ከመከላከሉም ባሻገር ዜጎች ባላቸው ሙያና የትምህርት ደረጃ/ ዝግጁነት ላይ ተመስርቶ ከፍተኛ የሥራ እድል እንዲፈጠርላቸው ያስችላል።

ለ.4. ባለፉት 30 ዓመታት የአዲስ አበባ ከተማ ወጣቶች አግላይ በሆነው የጎሳ ፖለቲካ በእጅጉ ሲማረሩ እንደነበር የአደባባይ ሚስጢር ነው። በመሆኑም የአዲስ አበባ የራስ ገዝነት መብት መረጋገጥ የከተማው ወጣቶችን ፍትሃዊ የኢኮኖሚ፣ የፖለቲካ እንዲሁም የማህበራዊ ተጠቃሚ እንዲሆኑ የኢኮኖሚ ሜዳውን ያመቻቻል።

ለ.5. የአዲስ አበባ የወደፊት ሁኔታ አጠራጣሪ በመሆኑ በሃገር አቀፍ ደረጃ ሰርቶ አገርን የማበልፀግ ስሜት በእጅጉ በመመናመኑ በኢኮኖሚው የወደፊት ሁኔታ እምነት የታጣበት (Economic Uncertainty) ሁኔታ ተፈጥሯል። በዚህ ምክንያት አዲስ አበባን ማዕከል ካደረገው የኢትዮጵያ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ መጠኑ እጅግ ከፍተኛ የሆነ የሃገር ገንዘብ ወደ ውጭ ሃገራት እየሸሸ ይገኛል። ይህ ገንዘብ ሃገሪቱንም ሆነ አዲስ አበባን በማልማት ረገድ በከፍተኛ ደረጃ ጠቃሚ ሊሆን የሚችል ሃብት ነበር። የአዲስ አበባ ራስ ገዝ መሆን ይህን የኢኮኖሚ እምነት የማጣት እና ገንዘብን ወደ ውጭ የማሸሽ ፍላጎት ለመቅረፍ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያደርጋል።

ለ.6. በሃገሪቱ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ የጎላ ሚና የሚጫወቱት እና በየክልሉ እየሄዱ የሚያለሙት የሃገሪቱ ባለሃብቶች የሚገኙት በአብዛኛው አዲስ አበባ ነው። በእነዚህ ባለሀብቶች አዕምሮአቸው ውስጥ የአዲስ አበባ የወደፊት እጣን በተመለከተ የጠራ ሁኔታ አለመኖሩ፣ በባለሃብቶቹ ዘንድ ኢኮኖሚ ውስጥ በሚታየው የተዛባ ፖሊሲ ሳቢያ የኢኮኖሚ ተነሳሽነታቸውን እንዲያጡ ያደርጋቸዋል። የዘውግ ፖለቲካ ውጤት የሆነው በ2012 ጥቅምት እና ሰኔ በመንጋ እርምጃ ምክንያት የደረሰው ከፍተኛ የህይወት እና የሃገር ሃብት ውድመት ባለሀብቶች ገንዘባቸውንና ተነሳሽነታቸውን በተግባር ላይ እንዳያውሉት በማድረግ የሃገሪቱን ኢንቨስትመንት በከፍተኛ ደረጃ የሚጎዳ ሆኗል። አዲስ አበባ ራሷን በራሷ ማስተዳደሯ ይህን መሰል የኢኮኖሚ እንቅፋቶችን ለመፍታት ድርሻው የጎላ ነው።

## ሐ/ በማህበራዊ ዘርፍ

ሐ.1. በአዲስ አበባ እና በመላ ኢትዮጵያ ንሮ የሚገኘው የምግብና የሸቀጣሸቀጥ ዋጋ መንግሥት ከሚከተለው የተዛባ የፋይናንስ ፖሊሲ፣ አገሪቱ ከሚያጋጥማት የእህል እጥረት ጋር የተዛመደ ቢሆንም፣ የአዲስ አበባ ቅጥ ያጣ የመሬት ዋጋ የኑሮ ውድነትን በማባባስ በኩል ከፍተኛ ሚና ይጫወታል። የአዲስ አበባን ራስ ገዝነት በማረጋገጥ የከተማው የመሬት ግብይት በሕግና በስርአት እንዲመራ በማድረግ ከፋይናንስ ፖሊሲው መስተካከል ጋር የዋጋ ንብረት እንዲቀንስና የኑሮ ውድነት ዝቅ እንዲል ያደርጋል።

ሐ.2. አዲስ አበባ የቀድሞ ስፋቷ ተመልሶ በተመለሰው ይዞታዋ ላይ የራስ ገዝነት መብቷ ቢረጋገጥ፣ ከተማ ቀመስ ግብርናን በማስፋፋት ከተማዋ በእህልና በአትክልት ምርት ራሷን እንድትችል ማድረግ ስለሚቻል፣ በአዲስ አበባ የሚገኘውን በሚሊዮኖች የሚቆጠር ሥራ አጥ እና ከፊል ሥራ አጥ ሥራ በማስያዝ የሃገሪቱ ኢኮኖሚ ዋነኛ ችግር የሆነውን የሥራ አጥነት ችግር በከፍተኛ ደረጃ ለመቀነስ ይረዳል።

ሐ.3. የአዲስ አበባ ራስ ገዝነት በአዲስ አበባ ውስጥ ያለውን ከፍተኛ የውሃ አቅርቦት ችግር በአዲስ አበባ ዙሪያ ያለውን ከፍተኛ የከርሰ-ምድር ውሃ በማልማት የከተማዋን በየጊዜው እየጨመረ የሚሄድን የነዋሪ ብዛት የውሃ ፍላጎት መታደግ ይቻላል።

## የሌሎች የፌዴራል ሃገሮች ዋና ከተሞች

## ተመክሮ

በዓለም አቀፉ ደረጃ የፌዴራል ስርአትን ከሚከተሉ አገሮች ልምድ አንፃር ካየነው ለአዲስ አበባ እየተጠየቀ እንዳለው እውነተኛ የፌዴራል አስተዳደር ዋነኛ መመዘኛ የሆነው ራስን በራስ የማስተዳደር መብት እንደሆነ ለመገንዘብ ይቻላል።

የሩሲያ ፌዴሬሽን ዋና ከተማ የሆነችው ሞስኮን ብንወስድ ሞስኮ የፌዴራል መንግሥቱ ዋና ከተማ መሆንዋ እንደተጠበቀ ሆኖ ሞስኮ ራሷን የቻለች የራስ ገዝ አስተዳደር ያላትና በበርካታ የገጠር ከተማ ቀመስ አስተዳደሮች የተዋቀረች ነች። ስያሜዋም (Greater Moscow Area) በመባል ይታወቃል።


ጥንታዊቷ በርሊንም የጀርመን የፌዴራል መንግሥት መቀመጫ ብትሆንም ከ16ቱ የጀርመን የፌዴራል ግዛቶች መካከል እንደ አንዷ ሆና የራስ ገዝ አስተዳደር መብት እንዲኖራት ተደርጓል። ልክ አዲስ አበባ በኦሮሚያ ክልል እንደተከበበች ሁሉ በርሊንም "ብራንድንበርግ ቡንደስላንድ" ክልል የተከበበች ናት። ይሁንና የከተማዋ ነዋሪ የራሱን ከንቲባ የሚመርጥባት እራሱን የቻለ አስተዳደር እና እንደሌሎቹ አሥራ አምስቱ የጀርመን ራስ ገዝ /ከተሞች የራሷ ግዛት ኖሯት የተዋቀረች ናት።

የአውስትራሊያ ፌዴራላዊ አገር ዋና ከተማ የሆነችው ካንቤራም የፌዴራል መንግሥቱ ዋና ከተማ እና ራሱን የቻለ (Australian Capital Territory) የሚል የግዛት መጠሪያ የተሰጣት ከተማ ናት። በዙሪያዋ ያሉትን ከተሞች ያካተተ የራስ ገዝ አስተዳደር ስልጣን እንዲኖራት ተደርጋ የተዋቀረች ከተማ ናት።

ከነዚህ የፌዴራል አገሮች ዋና ከተማዎች ልምድ በመነሳት አዲስ አበባም በታሪክ እና በሕግ የተደገፉ የራስ ገዝነት ስልጣን የነበራት ከተማ እንደመሆኗ የቀድሞ ስፋቷን መልሶ የፌዴራል አገሮችን ዓለም አቀፍ ልምድ ባገናዘበ መልኩ፣ የራስ ገዝነት መብት ልትጎናፀፍ ይገባል። የባልደራስ ለእውነተኛ ዲሞክራሲ ፓርቲ ይህን የአዲስ አበባ የራስ ገዝነት ጥያቄ ያንሳው እንጂ ጥያቄው ከጽንፈኛ ብሄረተኞች ውጭ በኢትዮጵያ በየትኛውም አካባቢ ያሉ የፖለቲከ ኃይሎች የሚደግፉት ጥያቄ እንደሆነ በመተማመን፣ ለጥያቄው መመለስ ከሁሉም የኢትዮጵያ የፖለቲካ ኃይሎች ጋር በጋራ ለመሥራት ዝግጁ መሆኑን ይገልፃል።

አዲስ አበባ በነዋሪዎቿ ህብረትና አንድነት እንዲሁም በቀደመ እውነቷ በጽንፈኛ የኦሮሞ ብሔረተኞች ከተጫነባት የሞግዚት አስተዳደር ነፃ ትወጣለች!!!

# የሃሳብ ልዩነት የችግር መፍትሔ ወይስ ምንጭ?



(በልስቲ ይስመው)

በህይወቴ ይችን ስንክሳር ዓለም ተቀላቅየ እዚህ ደረጃ እስከ ደረስኩበት ጊዜ ድረስ ለቅጥር አሻራ ለመነሳት ካልሆነ በቀር አንድም ቀን የፖሊስ ጣብያን ረግጬ አላውቅም:: ለአሻራ በሄድኩበት ቀንም መለዮ ለባሽ አይቼ የተነቀጠቀጥኩበት ጊዜ አልነበረም:: አሁን ግን የተለየ ነው:: በፌድራል መንግሥት ወይን ቤቶች ስር ውስጥ የሚገኘው ቃሊቲ ወይን ቤት ስደርስና ወደ ውስጥ ገብቼ ልፈተሽ ስዘጋጅ የነበረኝ የፍርሃት ስሜት በቃላት የሚገለፅ አይደለም:: የፍርሃቴ ምንጭ ደግሞ ለጠይቅ የሄድኩበት እስረኛ በቀርብ የማውቃት እና ሁሌም የሞራል ጀነሬትር የምትሆነኝ አስካለች ደምለው የባልደራስ ለእውነተኛ ዲሞክራሲ ፓርቲ ኮከብ አባል ነች:: ስለዚህ የባልደራስ አባል መሆን ብቻውን እንደ ወንጀል በሚቆጠር ሀገር የባልደራስ አባልን መጠየቅ ቢያስፈራ ኤደንቅም ምክንያቱም ከግዙፉ እስክንድር ነጋ ትክሻ ላይ ያረፉ የፖሊስ ጡንቻ እኔን አንድ ተራ ሰው ሊፈጨኝ እምደሚችል እጠረጥር ነበርና:: የታላቁን እስክንድር ነጋ ግዙፍነት የገለፅኩት በአካል ሳይሆን በአስተሳሰብ እንደሆነ ሊሰመርበት ይገባል:: እንደ ምንም ፍተሻየን በሰላም ጨርሸ እራሴን እንዳረጋጋም ፖሊሱቹ እገዛ አድረገውልኝ ወደ ውስጥ ገብቼ ወዳጀን ሳስጠራ ዘወትር ከፊቷ ላይ ፈገግታ የማይለያት አስካል ብርድስት ላይ ተጥዶ እንደሚፈላውሃ እየተፍለቀለቀች ብቅ አለች:: ለረዥም ጊዜ ተለያይተን ነበር እና ሞቅ ያለ ሠላምታ ከተለዋወጥን በኋላ አሁን ስላለው ሁኔታ እና ለእስር ያበቃትን ሁኔታ ስጠይቃት የሰጠችን ምላሽ አንድም አሳዝኖኛል:: አንድም አስቆኛል:: ሳቁም በሀዘን የተለወሰ ቢሆንም የጥርስዲሞ እንደሚሉት አባው:: በተመስጦ ውስጥ ሁና ያጫወተችኝን ቃል በቃል እንደሚከተለው አቀርበዋል::

እስካለች ደምለው ትባላለች ከአባቷ ከአቶ ደምለው ደሳለኝ እና ከእናቷ ዘውዱዓለም እንቢ አለ በ1983 ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ ጉለሌ ክፍለ ከተማ ልዩ ስሙ ቁስቋም በሚባል አካባቢ ተወለደች:: አስካለች ለቤተሰብ 4ኛ ልጅ ስትሆን እትብቷ በተቀበረበት አካባቢ ከእድሜ እኩዮቹ ጋር እንደማንኛውም የአዲስ አበባ ህበረሰብ ልጅ በእንክብካቤ እና በፍቅር በቤተሰብ እንክብካቤ አድጋለች:: እድሜዋ ለት/ት ሲደረስ ከኩዮቿ ጋር በመሆን ቁስቋም ጣይቱ ብጡል የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት አብርሃ ወፅብሀ የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት አምሀ ደስታ እና ኮተቤ ወንድ ይራድ ት/ቤት በመዘዋወር ስትማር ሁለተኛ ደረጃ ትምህርቷን ደግሞ በመነን ይካቴት 12 ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት አጠናቃለች:: በተፈሪ መኮንን ት/ቤት በዲፕሎማ አካውንቲግ የተማረች ሲሆን በጌጅ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ ደግሞ ዲግሪዋን በአካውንቲግ ሰርጣለች:: ወጣት አስካል ደምለው በወጣትነት ዘመኗ ብዙም ባትሄድበትም ከማህበራዊ ኃላፊነቷ ባሻገር የወጣትነት ጊዜዋን በስፖርቱ ዘርፍ እንጦጦ ተራራ ስፓርት ክበብ አትሌቲክስ ሰርታለች:: በኪነ - ጥበብ ዘርፍ ደግሞ የኮሌጅ ላይፍ በሚል ርዕስ የወጣው ፊልም ላይ ታምራዊ የትወና ብቃቷን አሳይታለች:: በይበልጥ በዚህ ፊልም ትታወቅ እንጅ በርካታ የተለያዩ ፊልሞችን በመሥራት ለዘርፍ የራሷን አሻራ አጉርፋለች::

ወደ ፓለቲካው እንዴት መጣሽ ተከታዮ ጥያቄ ነበር? በምኖርበት ሀገር ኢትዮጵያ በተለይ አዲስ አበባ ህዝብ ላይ ለልፋት 27 ዓመታት ውስጥ የነበረው በደል እና ስቃይ እንዲሁም ጭቆናን ለመረዳት በጥበብ ሙያ ውስጥ ከመኖሬም በላ የአዲስ አበባ ህዝብ የችግር /የጭቆና/ ጀራፍ እኔምም ጨምሮ ይገርፈኝ ነበርና ለመረዳት ቀላል ነበር:: እናም ያንን ዘግናኝ ስርዓት ለመገርሰስ እና ለመጣል ሀሳባቸው ከሃሳቤ ጋር ቅርብ ከሆኑ አካላት ጋር እንደማንኛውም ተራማጅ ወጣት ሲብሰከሰክ ነበር::

በመሰሪያ ቤትም ሆነ በመኖሪያ አካባቢና ከሚቀርቡኝ አካላት ጋር ይህ የጨለማ ዘመን ተገፎ የብርሃን ዘመን የሚመጣበትን ጊዜ በተስፋ እንጠብቅ ነበር::

ሆኖም የፈራነው ደረሶ ብናየውም በማይታመን መልኩ ከጫፍ እስከ ጫፍ ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር በሚል ለይስሙላ መፈክር የተታለለው ህዝብ ግልብጥ ብሎ በቄሮ እና በፋኖ ደም እና አጥንት የተገኘን ለውጥ የለውጥ መሪ ብለው የህዝብን ለውጥ በመንጠቅ ወደፊት ሲመጡ ድጋፍን ሲያሳይ እኔም ከህዝቡ ጋር የዚህ ሴራ ሰለባ ነበርኩ:: ለውጥ አለ መስሎኝም ለተወሰነ ጊዜ ከእነ ሙሉ ድጋፌ አምኘ ተቀበልኩት:: እየቆየሁ ስሄድ ግን ለውጡ በማር የተለወሰ መርዝ መሆኑን ለመረዳት የፖለቲካ ጠበብት መሆንን ወይም አምላክ መሆንን አይጠይቅም ምክንያቱም ማንም ነገሮችን ማስተዋል የሚችል ሰው በቀላሉ መረዳት ይችላል:: ለዚህ እናመሰል ነገሮች ወጣት አስካለች ደምለው እስከትላ ስትናገር በጋሞና በሲዳሞ ወጣቶች እና ህዝቦች ላይ የተሰራው ፓለቲካዊ ሴራ የደቡብ ህዝቦች መፍናቀል እና ጭፍጨፋ የአማራ ህዝቦች ጭፍጨፋ እና ጭቆና ከ27 አመት በ2 ዓመት ውስጥ ጎልቶ ሲታየኝ፤ ተረኛ ነን ባዮች ቆንጨራ፣ ሜጫ እና ዱላ ይዘው ሲወጡ መንግስታዊ ሽፋን ሲሰጣቸው በዶ እጃቸውን ይዘው ለሚወጡት የአዲስ አበባ ልጆች እና ሌሎች ከብሄሮች ግን ሁከት ፈጣሪዎች እየተባሉ ወደ ጦላይ መወርወርን እያየ ፡ የአዲስ አበባ ህዝብ ንብረት በጠራራ ፀሀይ ሲዘረፍ እያየ ህገ ወጥ የመሬት ወረራ ሲካሄድ እያየ ህገ ወጥ ስም ብሄርን ብቻ መሰረት ያደረገ ሰዎች ለአመታት ላባቸውን ጠብ አድርገው ያፈሩት ሀብታቸውን ለሊት እንደ ሽፋታ ሲያወድሙባቸው ቅርስ ሲወድም እና ሲፈርስ እያ የሀገር ታሪክ ሲጠለሽ እና ሲዘቅጥ እያየ በግንባታ እና በልማት ሰበብ የሀገር ሃብት ያለምንም ህጋዊ ጨረታ የህዝብ ሀብት ሲዘረፍ እያየ ለውጥ አለ የሚል አካል ካለ አንድም የተረኝነት አስተሳሰብ ያለው ሰው ነው በሌላ መንገድ ደግሞ ሳይካትሪስት የሚያስፈልገው መሆን አለበት::

ሁላችንም ቢሆን ከዚህ በኋላ በሃይ ባይ በጦርነት ሳይሆን የህዝብ ቅቡልነት ማግኘት የሚቻለው በሃሳብ የበላይነት ብቻ ነው:: ማንኛውም አካል ሀሳቡን ይዞ መጥቶ በጠረንጴዛ ዙሪያ ተወያቶ ሃሳብን በመሸጥ ብቻ የህዝብን ስልጣን መረከብ ይቻላል:: የሚል ጣፋጭ እሳቤውን አራምዶ የህዝብን ስሜት ከተቆጣጠረ በኋላ ብርቱ፣ ምጡቅ እና ባለተራማጅ ራዕይው በታላቁ እስክንድር ነጋ ለሠላ፣ ለፍትህ፣ ለእድገት፣ ለእውነተኛ ዲሞክራሲ እና ለህዝብ ደህንነት ዘላቂ የመፍትሄ ሀሳቡን በማቅረብ ህዝቡን በቀላሉ መማረኩን ሲረዳና አየር ላይ ተንሳፎ እንደሚቀር ሲገነዘብ ጦር እንማዘዛለን በማለት የሀሳብ ልዕልናን በቅፅፈት ወደ ጦርነት የሚቀይርን አካልን የለውጥ መሪ ነው የሚል ካለ::

ለ27 ዓመት ሙሉ ጭቆና ስርዓትን ያዳበረ እና አሁንም በጭቆና ቀበር ለመማቀቅ ራሱን ያዘጋጀ አካል መሆን አለበት:: የዚህን መንግሥት ችግር በቀላሉ መዘርዘር አይቻልም አውሎ ያሳድራል እና እንተወው ከመታሰርሽ በፊት ትግል ላይ በነበርሽበት ሰዓት የገጠመሽ ክስተት ካለ? ▶

ሁለተኛው ጥያቄ ነበር::

ተቀጥሪ የምሰራው በመንግሥት መስሪያ ቤት ነው:: ለዘጠኝ አመት ያህል አገልግያለሁ እዚያ በምሰራበት ወቅት አንድ ለአምስት የሚባል ክንውን አለ:: በዚህም መሰረት ማን የብልፅግና አባል ነው? ማን አይደለም ወይም ተቃዋሚ ነው የሚሉትን ጥያቄዎች በቀላሉ መመለስ የሚቻልበት የጥርነፋ ስልት ነው:: በዚህ የጥርነፋ ስልት እኔ የተቃዋሚ አባል መሆኔ ታወቀ:: ለዛውም ለመንግሥት የራስ ምታት ለሆነው ባልደራስ::

ራስምታት ስልህ መንግሥት ባልደራስን ስለሚፈራው ነው:: ምክንያቱም በጉልበት ካልሆነ በሃሳብ እና በፖለቲካ ገብያ ባልደራስን መቋቋም አይችልም:: እያደረገ ያለውም ይህን ስለሆነ ወደ ዋናው ነጥቤ ስመለስ ከዛ በኋላ ሁልጊዜም ቢሆን እኔ ላይ ክትትል ማድረግ ጀመሩ:: ሰበሰብ ብለን በተቀመጥንበት እኔን ለማሸማቀቅ ስለ እስክንድር መጥፎነት ማውራት፣ ሳለ ባልደራስ አሉታዊ ነገር መናገር:: በዚህ እንደማልበገርላቸው ሲረዱ ደግሞ በጥቅማጥቅም መጡብኝ:: በደረጃ እንድገት፣ በስልጠ፣ በቤት ወዘተ ይህም አልሆነ አለ:: በቁርጥ ከዚህ እንቅስቃሴ እንዳቆም ጥብቅ ትዛዝ ተሰጠኝ:: ካልሆነ ግን የመንግሥት ሥራየን እንደምለቅ በግልፅ ቋንቋ ተነገረኝ:: ከዚህም ጋር ያይይዞ በኮቴ ልክ በደህንነት ይከታተሉኝ ነበር፣ ሻይ ቡና ስንል በሰርቢስ እቤቴ ድረስ በመከተል:: በGPS ሀሰት አላፊ ቤቴ ድረስ እየመጡ ለማፈን ሙከራ አድርገዋል:: ስልኬን ጠልፈዋል:: አሁንም እስር ቤት ውስጥ እለሁ የእጅ ስልኬን ኢንተርኔትም ሆነ የስልክ ጥሩ እየተጠቀሙበት ነው:: ቀድሞ ቢሆን በስልኬ እየተደወለ ዛቻ እና ማስፈሪያ ይደርስብኝ ነበር:: ፎቅ ላይ በመሆን ፎቶ ያነሱናል:: ብቻ ብዙ ነው::

## እስር ቤት እያለሽ እጅሽ ከተያዘበት እስካሁን ድረስ ያለው አያያዝሽ ምን ይመስላል?

ማዕከላዊ እያለሁ ከቆጠራ በኋላ በመስኮት ለምስክርነት ያስጠኑኝ ነበር:: አስጠንተውኛል የሚልም ሙሉ እምነት አለኝ:: ቤተሰብ ሊጠይቀኝ ሲመጣ ይመልሱብኛል እዚህ ቃሊቲ እለሁም ቢሆን ለዚህ ሰለባነኝ ከዚህ የጎላ ነገር የለም::

ማዕከላዊ እለሽ የምረመራ ሂደትሽ ይዘት ምን መስላል ከምን አውድ ነበር የሚመረምሩሽ

ምርመራው እጅግ ያስቃል:: ምርመራውን ከምነግርህ የክሱን ይዘት እና አውድ ብነግርህ ይቀላል:: ምክንያቱም ምርመራውም ከክሱ ስለማይዝል:: ምን መሰለህ የተከሰስኩት አንደኛ የሚኒሊክን ሀውልት እንዳይፈርስ ተከላክለሻል፣ ሁለተኛ የአማራን እና የጋሞን ተወላጆችን አንድ በማድረግ አደራጅተሻል፣ ሶስተኛ የጦር ኃይሎችን ወጣቶች አደራጅተሽ በቄሮ ላይ ጥቃት አድረሰሻል የሚል ነው:: እንግዲህ ተመልከት አላደረኩም እንጅ ባደርገው ጥፋቱን መከላከል ጥፋትን ማዳን ወንጀል የመሆነበት ሀገር ህዝብን አንድ ማደረግ፣ ህዝብን ወደ አንድ ማዋሀድ፣ ልዮነትን ማጥበብ መተባበርን እና መደጋገፍን ማጎልበት እንደወንጀል ከተቆጠረ የኢትዮጵ ህዝብ ይቅጣኝ:: ጦር ኃይሎች ለተባለው እውነቱንም ሆነ ውሸቱን ድፍን የኢትዮጵ ህዝብ ባይስተውም ዳኝነቱን ግን ለፈጣሪ እና ለእግዚአብሄር በታች ድርጊቱ ተፈፀመበት የተባለው የአካባቢው ህዝብ ይፍረደኝ::


## አሁን እዚህ ድርጊት ውስጥ መግባትሽ እና ለዚህ ችግር ለመዳረግሽ ትፀፀቻለሽ?

አልፀፀትም፤ ምክንያቱም ምንም አይነት ወንጀልም ሆነ ጥፋት አልሠራሁም የታሠርኩበት ስሰርቅ፣ ንብረት ሳወድም፣ የሰው ነብስ ሳጠፋ የሰው ወንድ ሳማግጥ ህዝብን ከህዝብ ሳጋጭ፣ የሰው ነፍስ ሳጠፋ አይደለም:: እኔ የታሰርኩት ለምን የጭቁኖች ልሳን ሆንሽ ለምን ጭቆናችን አፀናናሽ ከባርነት ቀንበር እንዲላቀቁ ለምን አነቃሽ፣ ለመብት እንዲታገሉ ለመን ሰራሽ፣ እና ለግፍኞቹ እንደፈለገችን እንዳንሆን ለምን እንቅፋት ሆንሽን ተብየ ነው:: እና አልፀፀኩም:: እኔ የጀግና ልጅ ነኝ ጀግንነቴን ደግሞ የምገልፀው እንደነሱ ሰው በመግደል በማረድ ሀብትንብረት በማውደም እና በመዝረፍ አይደለም:: ለጭቁኖች፣ ለተከፉ፣ ላዘኑ፣ የሠላም እጦት ለአንገበገባቸው ፈጥኖ ደራሽ በመሆን እንጅ:: ተስፋቸ ተሟጦ በጨለማ ውስጥ ለሚደክሩ የተሰፋ ብርሃን በመሆን እንጂ:: በመንፈሴም ሆነ በስነ ልቦናየ እንዲህ አይነት አኩሪ የሆነ መንፈስ ሠረፆ እንዴት አፀፀታለሁ:: በፍፁም አልፀፀትም::

## ህዝቡ እንዲረዳሽ የምትፈልጊው ነገር ካለ?

የታሠርነው ለህዝብ ደራሽ ናችሁ ተብለን ነው እና የፍትህ ስደቱ የኢትዮጵ ህዝብ አመዛዝኖ እንዲፈርደን እንፈልጋለን ፍትህን የምናገኘው ከፈጣሪ በታች በህዝብ ነውና:: ሌላ አሁን ሀገሪቱ ያለችበትን ምስቅልቅል ሁኔታ ሁሉም ህዝብ ይገነዘባል የሚል እምነት አለኝ:: ለዚህ ሁሉ ደግሞ ዋናው ተጠያቂ አሁን በስልጣን ላይ ያለው መንግሥት ነው:: ከዚህ ችግር ለመውጣት ደግሞ ወጣቱ ትውልድ በተረጋጋና በሠከነ መንገድ ጠንክሮ መሥራት አለበት:: የዚህ ትውልድ ባላደራዎች ነን እና የጥንት አያት ቅድመያቶቻችን እና አባቶቻችን እንድነቷን እና ክብሯን አስጠብቀው እንዲቆዩን በሀገር በመጤ ብሄርተኝነት እና ዘረኝነት መንፈስ ልትበታትን ጫፍ ላይ የደረሰች ሀገር ወደነበረችበት የከፍታ ልዕልና መልሰን ለቀጣዩ ትውልድ እናስረክብ ዘንድ ያለምንም ብሄር እና ኃማኖት ልዩነት በመርህ እና በእውነት ላይ የመሰረተውን ባልደራስ ለእውነተና ዲሞክራሲ ፓርቲ ታዛ ስር በመጠለል ይህን ዘረኛ እና ፅንፈኛ ጨቋኝ አገዛዝ ከስሩ ለመጣል ቆርጦ መታገል ካለበት ድል ለእውነተኛ ዲሞክራሲ!

# ወንጀለኛው ማን ነው?



(አስካለ ደምሌ፤ ከቃሊቲ ወህኒ ቤት)

በዓለም ላይ የሀሳብ ልዩነት ወንጀል እንዳልሆነ የሚናገሩ መንግሥታት ብዙ ናቸው ብቻ ሳይሆን ሁሉም ናቸው ማለት ይቻላል:: ነገር ግን በተግባር ሲታይ የሃሳብ ልዩነት ያላቸው ሰዎች በልዩነታቸው ምክንያት ለእስር፣ ለሞት ለመፈናቀል፣ ለስደት፣ ሲዳረጉ ማየት የተለመደ ነው:: በተለይ የአፍሪካ መንግሥታት ይህንን ዋነኛ መገለጫቸው አድርገውታል::

ከፖለቲካ ፅንሰ ሃሳብ፣ ከህግ እና ከዓለም አቀፍ ስምምነቶ በተቃራኒ፣ የአፍሪካ መንግሥታት ዜጎች የሀሳብ ልዩነት እንዳይኖራቸው እያደረጉ ለአያሌ ዘመናት ሥልጣን ላይ ተንፈራጠው ቆይተዋል:: የሃሳብ ልዩነት ያላቸው የፖለቲካ ድርጅቶችን ማፍረስ፣ ጥገኛ እንዲሆኑ ማድረግ፣ እንዳይግባቡ ማድረግ ይባስ ብሎ መሪዎቹን ማሰርና መግደል ተጠናክሮ ቀጥሏል::

ፓርቲዎች አፍራሽ አዋጅ እየተዘጋጀላቸው ጭምር ፈርሰዋል:: መንግሥት ገንዘብና የሰው ኃይል መድቦ በስውር ለማፍረስ ጥረት እንደሚያደርግ መረዳት ከባድ አይደለም:: ባልደራስ ለእውነተኛ ዲሞክራሲ ፓርቲም የዚህ ሰለባ እየሆነ ነው:: ከፍተኛ አመራሮቹን በማሰር ለማጥቃት እየተሞከረ ነው:: በተጨባጭ የሀገራችን ኢትዮጵያ ሁኔታ ብንመለከት ባለፉት 30 ዓመት ዜጎችን በሀሳባቸው ልዩነት ምክንያት ለእስር፣ ለሞት፣ ለስደት ሲዳርግ ቆይቷል፤ ስርዓቱ፡ አሁንም እየቀጠለ ነው:: በሀገራችን ኢትየጵያ ዜጎች በፖለቲካ ልዩነት ምክንያት የሚሞቱት ትክክለኛ ቁጥር ቢሰላ አስደንጋጭ አሀዝ እንደምናገኝ ጥርጥር የለኝም:: በተለይ በየክብረ በዓላት፣ በየወህኒ ቤቱ፣ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት እና በመሳሰሉት ውስጥ የሚሞቱት ዜጎች ብዛት የሚመለከተው አካል ዳታ ከፍተኛ ነው:: በዚህ አጋጣሚ ቁጥሩ በትክክል ተጠንቶ እንዲቀርብ እጠይቃለሁ:: በፖለቲካ አመለካከት፣ በማንነትና በሃይማኖት ልዩነት የሚሞቱ ዜጎች ቁጥር በዓመት ከ4000 እስከ 5000 እንደሚደርስ እገምታለሁ::

በሃሳባቸው ልዩነት ምክንያት ለእስር፣ ለሥራ ማጣት፣ ለስደት የሚዳረጉ ዜጎች ደግሞ በዓመት በአማካኝ ከ18000 – 21000 እንደሚደርሱ ይገመታል:: በጣም የሚገርመው ግን ኢትዮጵያ በተለያዩ ጊዜያት እና ዘመናት የፖለቲካ አውድ ፊት ትግል ሲደረግ ቢቆይም በትግል አስቦ ሥልጣን የሚቆናጠጡ መሪዎች ልክ በህዝብ ትግል ሥልጣን እንደያዙ ረስተው ሀገሪቷን ለችግር እየዳረጉ እንዲኖሩ ከተማሪዎች ትግል እስከ አሁን ህዝባዊ ትግል ድረስ ያለው ታሪክ ማስረጃ ነው::

ብዙ ትምህርት፣ እውቀት ማስፈለጉ እንደ ተጠባቂ ሆኖ ታማኝነት ያለው እና ከግል ከፍላጎት የፀዳ መሪ ለኢትዮጵያ ያስፈልጋታል::

የሀሳብ ልዩነት ለአንድ ሀገር እድገት ከፍተኛ ጠቀሜታ እንዳለው ዓለም ይግባባበታል:: የድህነት ምንጭ ብዙ ነገሮች ቢሆኑም ዋነኛው ግን የሃሳብ ልዩነታችንን አለማክበር፣ አለመቀበል፣ ልዩነትን እንደ ጠላት ማየት ነው::

ስለዚህ አንድ የኢትዮጵያ ባለ ውለታ ነኝ የሚል ኢትዮጵያዊ፣ ኢትዮጵያን የሃሳብ ልዩነትን፣ የሃይማኖት ልዩነትን፣ የብሔር ልዩነትን፣ ለማስፋት መሞከር እራሳችንና ሃገራችንን የሚጎዳ መሆኑን በሚገባ በመረዳት ልዩነት ያለ የሚኖር መሆኑን መቀበል፣ በእኩልነት ማመን፣ ሁሌም ልዩነትን እዲያሰሙ መፍቀድ ትልቅ ውበት ነው::

አሁንም ፖለቲከኞችን በልዩነታቸው ምክንያት ማሰር፣ ምርጫ እንዳይሳተፉ ማድረግ ያለውን ችግር ከማባባስ በተጨማሪ ሌላ የማንግባባበት አጀንዳ መፍጠር ስለሆነ በፍጥነት እልባት ሊበጅለት ይገባል::

ማሰብ በፈጣሪ በነፃ የተሰጠ ችሮታ እንጂ መንግሥታት ሲፈልጉ የሚሰጡን ሳይፈልጉ የሚነሱን አይደለም:: የአፍሪካ መንግሥታት ተፈጥሯዊ መብቶች ለመከልከል ሲሞክሩ በጉልህ ይታያል:: ይህ ደግሞ ለሰፋ አለመግባባት፣ ሞት፣ እስር ዳርጎናል:: ከዚህም የዘለለ ለከፋ ጦርነት፣ ርሃብ እና መጥፎ ገፅታ ላለው ታሪክ እንድንጋለጥ አድርጎናል::

ሃሳብ ሀብት ነው፣ ልዩነት ያለ የሚኖር ነው፣ ልዩነትን ማጥፋት አይቻልም:: ይልቁንስ ሃሳብን፣ ልዩነትን በአግባቡ መምራት ስኬታማ ያደርጋል:: ምንጊዜም ማድረግ ያለብን የጋራ ነገሮችን መገንባት፣ የጋራ ነገሮች እንዲኖሩን ተግተን መሥራት ነው:: አንድነታችንን በማሳደግ ወደ ብሔራዊ መግባባት መቅረብ ይቻላል:: ዋጋውም ከፍተኛ ነው::

ልዩነት ተፈጥሯዊ እንደመሆኑ መጠን ልዩነትን በእስርና በመሳሰሉት ለመፍታት ያሰቡት መንግሥታት የጊዜ ጉዳይ እንጂ መዋረዳቸው አይቀርም:: ልዩነትን መቀበል እና በአግባቡ መምራት ዘመናዊነት ነው::

በአጠቃላይ የሃሳብ ልዩነቶቻችን እንደ ወንጀል ተቆጥረው ነው እስር ቤት የተወረወርነው:: ልዩነት ወንጀል ሊሆን አይገባም:: ይልቁንም ‹እንደ እኔ ካላሰባችሁ› ብሎ ሰዎችን በሃሰተኛ ክስ ማሰር ታሪክ ይቅር የማይለው ወንጀል ነው:: መንግሥታዊ ሥልጣንን ለእንዲህ አይነቱ ተግባር ማዋልም የወንጀል ወንጀል ነው::

# ኢትዮጵያዊ ኦሮሞነታችን የት ነው?

**(ጌንመ ዘብሔረ አዲስ አበባ )**

ዛሬ በውስጤ ስለሚብሰለሰለው የኦሮሞ ማንነት ጉዳይ እንነጋገራለን:: ሀሳቡን ከእኔ የተሻሉት ደግሞ አዳብረው ቢያቀርቡት ትልቅ ትርፍ ይኖረዋል ብዬ አምንለሁ::

ኦሮሞነት በሁለት ይከፈላል:: እነርሱም ኢትዮጵያዊ ኦሮሞነትና ባንዳዊ ኦሮሞነት ነው:: ኢትዮጵያዊ ኦሮሞነት ሀገር በቀል የሆነ ጥርት ያለ ኢትዮጵያዊ ሲሆን ባንዳዊ ኦሮሞነት ደግሞ መነሻውን ኢትዮጵያን ሊያፈርሷት ከሚፈልጉት ከነ ግብፅ ፣ ጣሊያን ፣ አረቦችና አውሮፓዎች ያደርጋል::

## እነዚህን ማንነቶች በሰው ማንነት መግለፅ ቢፈለግ፡-

1. ኢትዮጵያዊ ኦሮሞነት በጀግናው አርበኛ ጣሊያንን ባርበደበደው ሥመ ጥሩው ጀነራል ጃገማ ኬሎ ይመሰላል::

2. ባንዳዊ ኦሮሞነት ደግሞ በጎጠኛ ባንዳው ከሱማሌ እና ከወያኔ ጋር ባደረው የውጭ ጠላት ተላላኪው በዋቆ ጉቱ ይመሰላል::{c

እነዚህ ሁለቱም ኦሮሞነቶች የየራሳቸው መገለጫዎች ሲኖራቸው በዝርዝር ብዙ ማንሳት ቢቻልም ለዚህች ትንሽ ጽሑፍ ውስን ሀሳቦች ብቻ ላንሳ:: ለምሳሌ የኢትዮጵያዊ ኦሮሞነት መገለጫው በሀገሩ ጉዳይ አለመደራደር ፣ ለባንዲራውና ለሀገሩ ቀናዒ መሆን ፣ ታማኝ፣ ሀቀኛ ፣ ወገኑን እጅግ የሚወድና ከኢትዮጵያዊ ወገኖቹ ጋር በጋብቻም ይሁን በዝምድና መተሳሰርን የሚወድ ፣ ለወገኑ የሚሞት ሲሆን በተቃራኒው ደግሞ የባንዳዊ ኦሮሞነት መገለጫው ከጠላት ጋር የሚተባበር፣ ገንዘብ ወዳጅ፣ ኢትዮጵያንና ባንዲራዋን የሚጠላ፣ የበታችነት ስሜት ያለበት፣ ቂመኛ፣ በቀለኛ፣ ዘራፊ፣ ሁሉ ለእኔ ብቻ የሚል፣ ወገን ጠል የሆነ፣ ሀገር ቢበተን ምንም የማይመስለው፣ የሚጠላ፣ የበላይ ሆኖ መኖር የሚመኝ እና ሁሉንም መሰልቀጥ የሚፈልግ ነው::

አሁን በሥልጣን ላይ ያለው የኦህዴድ ብልፅግና/ ኦሮሙማ/ እና ኦነግ ከሁለቱ የኦሮሞነት መገለጫ ተነስተን ስንመዝነው የባንዳዊ ኦሮሞነት ባህሪ ውስጥ ሆነው አናገኛቸዋለን::

በዚህ ጽሑፍ ማንሳት የፈለኩት ከባንዳዊው ኦሮሞነት ባህሪ ውስጥ ሁሉን የመሰልቀጥ አባዜው መሃከል ኢትዮጵያዊ ኦሮሞነትን ለመሰልቀጥ እየሄደበት ያለበት መንገድን ነው::

በጣም የሚገርመው የባንዳዊው ኦሮሞነት የመሰልቀጥ አባዜ ምንም ሀፍረት ሳይሰማው ኢትዮጵያዊ ኦሮሞነትን በኦሮሞ ስም አንድ ነን በሚል የተምታታ የሀሰት ትርክት ለመሰልቀጥ እየሄደ ያለበት ርቀት ነው:: በምን መንገድ ይሆን ዘይት እና ውሃ የሚቀላቀለው ? በምንስ መንገድ ይሆን ጀግናው በአርበኛው ጀነራል ጃገማ ኬሎ ከባንዳዊ ዋቆ ጉቱ ጋር የሚቀላቀለው?

ነገር ግን ኢትዮጵያዊ ኦሮሞነትን ለራሱ መሰልቀጥ የሚፈልገው ቡድን በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ የጎላ ሚና የተጫወቱትን ኦሮሞዎችን ሥማቸውን ብቻ በመውሰድ እነርሱ ለሚፈልጉት የፖለቲካ ቁማር አካል ሊያደርጋቸው ሲሞክሩ እና የልጅ ልጆቻቸውን ኢትዮጵያዊ ኦሮሞዎችን ሊያምታቱበት ሲሞክሩ ይስተዋላል:: ይህም ማለት ለኢትዮጵያዊ ኦሮሞነቱ እነርሱ በሚፈልጉት የባንዳዊ ኦሮሞነት ጠባብ ልብስ አሰፍተው ሊያለብሱት ሲሞከሩ ይታያል::

ለምሳሌ፡- በዘንድሮው በ125ኛው የአድዋ በዓልን የጀግናውን የአርበኛውን የሥመ ጥሩውን የደጃዝማች ባልቻ አባነፍሶ ፎቶ ለጥፎ በክልል ደረጃ በሚል የልጆች ብልጣብልጥነት አ/አ ላይ  አክብረውታል:: ይህንን ሲያደርጉ ዓላማቸው አርበኛው አባታችን ከተሰለፈለት ዓላማ በተቃራኒው በሆነ ታሪክ በራሳቸው የባንዳነት ዓላማ ባለው ልብስ አሰፍተው ሲያለብሱት አስተውለናል:: ለሀገሩ ለእምዬ ኢትዮጵያ የተጋደለውን “ ገበየሁ ቢሞት ተተካ ባልቻ ፤ መድፍ አገላባጭ ብቻ ለብቻ “ ተብሎ የተገጠመለትን ሀገር አቀፉን ጀግና የኦሮሞነት ስብዕና ብቻ በማልበስ በኦሮሞነቱ ነው ድል ያደረገው በሚል መንፈስ የተዛባ ታሪክ ለመፍጠር ሲውተረተሩ ይታያል::

ጀግናው አርበኛው ደጃዝማች ባልቻ አባነፍሶ የሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል በጣሊያን ወራሪ ሲወረር ዘራፍ ብሎ ሄዶ የተዋጋ እና ድልም ያደረገ ኢትዮጵያዊ ኦሮሞ ነው:: ነገር ግን አነጋዊው የኦሮሙማው ብልፅግና የሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል በሱዳን ተወርሮ እያየ ሀገረ መንግስቱን ይዞ የናንተ ችግር የኔ ጉዳይ አይደለም ብሎ ይህው ቁጭ ብሎ ይመለከታል:: የነገ የታሪክ ተወቃሽነት ከቶ አያስጨንቃቸውም:: ሀገርን ለማስተዳደር ቦታ ይዞ ከመንደሩና ከጥቅሙ በላይ ማሰብ አይችልም:: ይሄ ነው እንግዲህ ባንዳዊ ኦሮሞነት ማለት ለሀገር የማይጠቅም ድኩማንነት::

በሌላ በኩል ደግሞ ጣሊያንን ያርበደበደዉን የሀገር እና የአፍሪካ ኩራት የሆነውን የሥመ ጥሩውን የጀግናውን እና የአርበኛውን የጀነራል ጃገማ ኬሎን ሥም ከቶ ማንሳት አይፈልጉም፤ ሥራውንም መዘከር ደግሞ እጅግ በጣም የሚፈሩት ጉዳይ ነው::

ጀነራል ጃገማ ኬሎ ስለ ኢትዮጵያ አውርቶ የማይጠግብ ባንዲራዋን ለብሶ ውሎ ለብሶ ቢያድር የሚወድ፣ ስለ ሀገሩ የሚቆጭ፣ ስለ ወገኑ የሚቆረቆር፣ ትዉልዱን ሀገራችሁን ውደዱ ጠብቁት ለእርሷም መስዋዕት መሆን ካለባችሁ መስዋዕት ሁኑላት ብሎ የሚመክር ፣ ሆኖም ያሳየ፣ ስለ ኢትዮጵያ ሀገሩ የሚዘምር ታላቅ አባት ሆኖ ሳለ ስለ እርሱ አንድ ነገር ማንሳት የሞት ሞት ነው የሚሆንባቸው::

በተቃራኒው ባንዳዊ ኦሮሞው ዋቆ ጉቱ ደግሞ ከጠላቶቻችን ከወራሪው የሱማሌው ዚያድባሬ ጦር ጋር በማበር በባሌ በኩል ሀገርን እያስመታ እና ጦር አደራጅቶ ወገንን እያስጨረሰ ብዙ መከራ ፈፅሟል:: ዐላማውም የባንዳዎች ሀሳብ የሆነውን ኢትዮጵያን የመበታተን እና የማፈራረስ ህልም ተፈፃሚ በማድረግ ኦሮሞን ከተቀረው የኢትዮጵያ ወንድሞቹና እህቶቹ መነጠል ነበር:: ኢትዮጵያንም ለማዳከም በ1950ዎቹ በሱማሊያ ውስጥ ስልጠና የወሰደ፣ ከወያኔ ጋር አብሮ ይሠራ የነበረ እና የመጀመሪያ የኦነግን ባንዲራ በባሌ ጫካ ውስጥ ያውለበለበ እርጉም የባንዳዊ ኦሮሞነት ተምሳሌት ነበር:: በኋላም በጀግናው ጀነራል ጃገማ ኬሎ የተማረከ መሆኑ ይታወሳል:: ነገር ግን ለዚህ ሰው ሀዉልት አቁመዉለታል፣ በስሙ ት/ቤት ፣ ባንክ እየሰየሙ ትልቅ ጀብድ እንደሠራ ሲክቡት ይስተዋላል::

አሁን በሥልጣን ላይ ባለው የኦሮሙማ መራሹ መንግሥት እየሆነ ያለው ግብዎች ፣ አረቦችና ነጮች እንደ እቅድ የያዙትን ኢትዮጵያዊ ኦሮሞነትን እና ኢትዮጵያዊ ማንነትን ከኢትዮጵያ ምድር ማጥፋትን እና ባንዳዊ ኦሮሞነትን በኦሮሚያ ምድር በማንገስ የኢትዮጵያን ታሪክ አበላሽቶ ሀገርን መበታተን ነው:: እንደ ዋና ዓላማ አድርገው እየተንቀሳቀሱበት ያለው ኢትዮጵያዊ ኦሮሞዎች የተሰውለትን እና የሞቱለትን ዓላማ በማዳከም ታሪክ የሠሩትን ሰዎች ሥም እና ዝና ብቻ በመውሰድ እነርሱ በሚፈልጉት የባንዳነት ልኬት መስፋት ሲሆን ሀገር ብለው ከደቡብ ሰሜን ከምዕራብ ምሥራቅ በእግር ተጉዘዉ ሀገር ለመታደግ የተጠቀሙበትን ዓላማና ፍቅር ሳያነሱ ስማቸውን ብቻ በመውረስ ተግባራቸውን መሰልቀጥ ነው::

ሌላኛዉ ደግሞ ኢትዮጵያዊ ሀገር ወዳድ አርበኛ ኦሮሞዎችና ቤተሰቦቻቸውን በማሸማቀቅ የመሰልቀጥ ፖሊሲያቸውን እያራመዱበት ያሉት መንገድ ስንመረምር ዛሬና ነገ ተከታይ አርበኛ ትውልድ እንዳይተካ የወጠኑት የዱኩማን አስተሳሰባቸው አካል መኾኑን እንረዳለን::

ስለዚህ እናንት ጊዜ የሰጣችሁ የወያኔ ምትክ የሆናችሁ የረከሰ አነጋዊና ኦህዴዳዊ ብልፅግና የጎሳ ፖለቲካ ቁማርተኞች፤ ንብረት፣ ቁሳቁስና ባንኮችን እንደምትዘርፉት ሁሉ የኢትዮጵያዊ ኦሮሞነትንም ከእምዬ ኢትዮጵያ ምድር ላይ ለማጥፋት እየሠራችኹ መሆኑን ሁሉም ኢትዮጵያዊ ተገንዝቦታል:: እየዘረፋችሁ ያላችሁትን ኢትዮጵያዊ ኦሮሞነታችንን ብትመልሱልን ይመረጣል::

ከዚህ በኋላ እኛ ኩሩ ኢትዮጵያዊ ኦሮሞዎች ትግላችን ከነ ደጃዝማች ባልቻ አባነብሶ ከነ ጀነራል ጃገማ ኬሎ ከአያት ቅድም አያቶቻችን የወረስነውን ኢትዮጵያዊ  ኦሮሞነታችንን ማስመለስና ማስጠበቅ እንዲኹም  እምዬ ኢትዮጵያ ሀገራችንን በጋራ ማቆም ይኾናል!!!

ኢትዮጵያ በልጆቸ ታፍራ እና ተከብራ ለዘላለም ትኑር!!!!

# ግልፅ ደብዳቤ ለአቶ ደመቀ መኮንን



ጌጥዬ ያለው

### ሱዳኖች ኢትዮጵያውያን የጉልበት ሠራተኞችን በእሳት ስለ ማቃጠላቸው

‹ሰዎች ለሰዎች› የተሰኘው የጀርመኑ ተራድኦ ድርጅት በተለያዩ የኢትዮጵያ አካባቢዎች ትምህርት ቤቶችን፣ የጤና ተቋማትንና ሌሎች የመሠረተ ልማት አውታሮችን ሠርቷል:: በዚህም መሥራቹ ካርል ሄንዝ በሕዝብ ዘንድ ተወደዱ:: ታዲያ በአንድ የምርጫ ወቅት ኢሕአዴግ ‹ነፍጠኛ› እያለ ሲጨቁነው ወደ ኖረው የሸዋ አማራ የ‹ምረጡኝ› ቅስቀሳውን ይዞ ሄደ:: በወቅቱ የመርሐቤቴ ሰው ‹ካርል የሚወዳደር ከሆነ እርሱን እንመርጣለን:: ከእርሱ ውጭ ምርጫ የለንም› ማለቱን የሰማሁት እኔ ብቻ ነኝ የሚል ግምት የለኝም:: ክቡር አቶ ደመቀ መኮንን እርስዎም ሰምተው እንደሚሆን እገምታለሁ:: እንዲያውም ከእኔ ወፏ ነገረችኝ ዓይነት ወሬ ይልቅ እርስዎ በሪፖርት ደረጃ የተጠናቀረ መረጃ ከበታች ካድሬዎችዎ ደርስዎት ይሆናል:: ኸረ እንዲያውም ‹ካርል የሚባል ሶላቶ ከኢትዮጵያ ምድር ጠራርገን እናስወጣልን› የሚል ድርጅታዊ ግምገማም አድርጋችሁ ይሆናል:: ከእናንተ መካከል ‹ካርል ሄንዝን የኢሕአዴግ እጩ ተወዳዳሪ እናደርጋለን:: የተመራጭ ሕጉንም እናሻሽላለን› ያለ ካድሬም ይኖር ይሆናል:: እርስዎ ኖት የሚያውቁት::

ይህንን ያስታወስኩት ጎንደርን ባሰብኩ ጊዜ ነው:: በዚህ በእርስዎ የምክትል ጠቅላይ ሚንስትርነት ብቻ ሳይሆን የውጭ ጉዳይ ሚንስትርነትም ዘመን ሱዳን የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት ገርስሳ ገብታለች:: ካለፈው ጥቅምት ወር መጨረሻ ጀምሮ እስከ አሁን ከዕለት ዕለት ምሽጎቿን እያበዛች እና ወደ መሀል ጎንደር እየገሰገሰች ነው:: ዘመናዊ የቡድን እና የነፍስ ወከፍ የጦር መሳሪያዎችን የታጠቀ ሰራዊቷ ኢትዮጵያን የወረረው በመንግሥትዎ መልካም ፈቃድ እንደሆነም የሱዳን ከፍተኛ የመንግሥት ባለሥልጣናት እየተናገሩ ናቸው:: በርግጥ በዚህ ጉዳይ ላይ ቃል አቀባይዎ ዲና ሙፍቲ አለቃዎ አብይ አሕመድ የወለፈቱትን ለማስተስርይ ሞክረዋል:: ማስተባበያውም ቢሆን አልሸሹም ዞር አሉ ነው:: የሱዳን ወታደሮች የጎንደርን ገበሬዎች ከዕለት ዕለት ይበልጥ እያፈናቀሏቸው ነው:: አዝመራቸውንና ከብቶቻቸውን እየዘረፏባቸው ነው:: ሰዎችን አፍነው እየወሰዱ ነው:: በተለይም ከሰሞኑ አሚራ ሀውልት ተብሎ የሚጠራው አካባቢ ላይ አፈና እና እገታው እንደ ሰሞነኛው የምርጫ ቅስቀሳችሁ ደርቷል:: ታግተው ከተወሰዱት መካከል ሻምበልና ይልቃል የተባሉ ኢትዮጵያውያን ይጠቀሳሉ:: የጉልበት ሠራተኞች ተገድለዋል:: ከእነዚህ መካከል በተለይ በሱዳን ወታደር ተገድለው በሳር እሳት ተለብልበው አስክሬናቸው የተቃጠለ ሁለት ሰዎች ጉዳይ አሳዛኝ ነው:: ይህ ሲሆን የእርስዎ መንግሥት ዜጎቹን ለማዳንም ሆነ ሉዓላዊነቱን ለማስከበር ምን አደረገ? የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት ለብሔራዊ ምስጢርነቱ ስል ቁጥሩን የማልገልፀው ሠራዊት ደለሎ እና አብደራፊ ላይ እንዳለው አውቃለሁ:: ከመከላከያ በተጨማሪ የዐማራ ልዩ ኃይል እና የፀረ ሽምቅ ታጣቂዎችም በዚያው እንዳሉ ሰምቻለሁ:: ታዲያ ይህ ኃይል ሀገሩንና ዜጎቹን የሚከላከለው መቼ ይሆን?

አቶ ደመቀ ሆይ፤ የሱዳን መንግሥትና ሠራዊት ‹ቤንሻንጉል ጉምዝ የእኛ ነው› እስከ ማለት ደርሰዋል:: ሠራዊታቸው ጎንደር ከተማ ድረስ ያልዘለቀውም በዐማራ ፋኖ መካችነትና ጀግንነት እንደሆነ ጎንደር በሰነበትኩባቸው ጊዜያት ተረድቻለሁ:: ሀገር እየጠበቀ ያለው እርስዎ የሚያዙት በሬ የሚቀልቡት መከላከያ ሳይሆን በሶ እየጠጣ በዱር በገደሉ የሚንከራተተው ፋኖ ነው:: የዐማራ ሕዝብ ‹ፋኖ የሚወዳደር ከሆነ እንመርጣለን:: ከፋኖ ውጭ ምርጫ የለንም፤ ወግድ›› ቢል ከካርል ታሪክ ተለይቶ የሚታይ አይደለም:: ይህ ሕዝብ ብልፅግና ፓርቲ በመፈንቅለ መንግሥት ከተወገደው የኡማር አልበሽሩ ብሔራዊ ኮንግረስ ጋር ቢምታታበትስ ጥፋቱ የማን ነው? መቼም እርስዎ ብዙ የምርጫ ዘመኖችን ስላሳለፉ ይህንን በደንብ የሚረዱት ይመስለኛል:: የምርጫውን ጉዳይ ለዛዲግ አብርሃ ልተወውና እንደ ውጭ ጉዳይ ሚንስትርነትዎ ወደ ሱዳን ወረራ ልመልስዎ፡-

ከመተማ ከተማ ወደ ሰሜን አቅጣጫ 20 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ የመነኩሴዋ ሻይ ቤት የሚባል ቦታ አለ:: በእዚህ ቦታ የካቲት 17 ቀን 2013 ዓ.ም. ከቀኑ ዘጠኝ ሰዓት ገደማ አቶ ሞላ ደስታ የተባሉ ባለንብረት ታግተው ተወስደዋል:: በጎቻቸው፣ ላሞቻው እና አህዮቻቸው ተዘርፈዋል:: የሱዳን ወታደሮች እረኞችን እና በአካባቢ የተገኙ የጉልበት ሠራተኞችን ሁሉ አፍነው ወስደዋል:: ተስፋዬ ወርቁ፣ መልካሙ፣ ለምለም፣አደራጀው የተባሉ ባለሀብቶች ሁሉ ጉዳት ደርሶባቸዋል::

ከመተማ ከተማ በግምት ከመቶ እስከ አምሳ ሜትር ርቀት ላይ የሚገኘውን ገለባት ከተማን የሱዳን ሠራዊት እየጠበቀው ነው:: ከተማው ውስጥ ምሽጎች ሠርቷል:: ከተማዋን ከሚከፍለው አስፋልት መንገድ ግራና ቀኝ ምሽጎች አሉት:: ከዚህ ጀርባ ደግሞ ሌላ ሦስት ምሽጎች አሉ:: አንደኛው ጠቅላላ ምሽግ ነው:: ይህ ቅይጥ ጦረኞች ያሉበት ነው:: ሁለተኛው የእግረኛ ምሽግ ሲሆን ሌላኛው ደግሞ የሜካናይዝድ ማዕከል ሆኗል:: የሱዳን ሠራዊት ይህ መረጃ እስከተጠናቀረበት ጊዜ ድረስ በምዕራብ ጎንደር በኩል ከወረራቸው ቦታዎች መካከል አብደራፊ፣ አቦጥር፣ ኮረድም፣ ኮር ሁመር፣ ስናር ተራራ (ሱዳን ግዛት ውስጥ ያለው ስናር ከተማ እንዳይመስሎት:: ይሄ ተራራ፤ ያ ከተማ፣ ይሄ ጓንግ ወዲህ ማዶ፤ ያ ጓንግ ወዲያ ማዶ፤ አይገናኙም)፣ ደለሎ ቁጥር 1፣ ደሎሎ ቁጥር 2፣ ደለሎ ቁጥር 3፣ ደለሎ ቁጥር 4፣ ደለሎ ቁጥር 5፣ ማሩ ሻይ ቤት፣ አዲስ ዓለም፣ ኮርጃ ሀሙስ፣ መነኩሴዋ ሻይ ቤት እና ቄሱ ሻይ ቤት ይጠቀሳሉ:: ከመተማ ደቡብ ክፍል ደግሞ ምንዳያና ፎርጊና ተወረዋል:: ቲሃ ውስጥ ስኳር ተራራ (ሱዳኖች ጀበል ስኳር የሚሉት)፣ ቋራ ቁጥር 2 ና ቁጥር 2፣ ኪዳነ ምህረት እና ነፍስ ገበያ የወራሪው ሰራዊት መዳረሻዎች ናቸው::

ሱዳኖች በክረምት ወቅት ለመንቀሳቀስ እንዳይቸገሩ ጓንግ ወንዝ (ሱዳኖች አትባራ ይሉታል) ላይ እስከ አብደራፊ ድረስ ስድስት ድልድዮችን እየገነቡ ነው:: አንደኛው ድልድይ

ፍንዱስ ላይ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ከፍንዱስ በላይ ነው:: በረከት ላይ፣ አሲራ ላይ እና ባሕረ ሰላም (አቦጥር) ላይ ሌሎች ድልድዮች እየተገነቡ ናቸው:: በተጨማሪም የጓንግ እና የአንገረብ ወንዞች መገናኛ ላይ ሌላ ድልድይ ተጀምሯል:: የሱዳን መሪዎች በየጊዜው በሄሊኮፍተር እያረፉ የኢትዮጵያን መሬት በሸንሸና ለገበሬዎቻቸው እያከፋፈሉ ነው:: በየቀኑ ግዛታቸውን እያስፋፉ ናቸው:: ለዚህ ደግሞ ወያኔ ለዘመናት አስፍሯቸው የኖሩ የትግራይ ባለሀብቶችም ጭምር ተባባሪዎች ናቸው:: የእርሻ ማሳቸውን በፈቃዳቸው እየለቀቁ ሱዳን ኢትዮጵያን እንድትወር መንገድ መሪ ሆነዋል::

በነገራችን ላይ ይህ ወረራ ሱዳን በየዓመቱ በኢትዮጵያ ላይ ከምታደርገው ትንኮሳ የተለየ ነው:: የተለመደውን ዓይነት ወረራ ባለፈው ዓመት በተለይ በግንቦት ወር በተጠናከረ ደረጃ አድርጋለች::

በዚህም ታጣቂ ቡድኑ ጓንግን ተሻግሮ የኢትጵያ ግዛት ውስጥ ኮረዲም፣ ምድሪያ፣ ግራር ውሃ የተባሉ ቦታዎችን ተቆጣጥሮ ነበር:: የተለያዩ የዐረቡ አለም መገናኛ ብዙሃን ደግሞ ኢትዮጵያ ለሱዳን ለም የእርሻ መሬት ለመስጠት መስማማቷን ዘግበዋል:: ከእነዚህ መካከል አሽራክ አልሳውት የተባለው ጋዜጣ ጉዳዩን በስፋት አስነብቧል:: እንደ ጋዜጣው ዘገባ ኢትዮጵያ በ1995 ዓ.ም በአቶ አባይ ፀሐዬ ፊታውራሪነት ከተሰጠው በተጨማሪ 600 ስኩየር ኪሎ ሜትር ለም የእርሻ መሬት ለመስጠት መስማማቷን ፅፏል:: የመሬት እርክክቡም በሁለት ሳምንታት ጊዜ ውስጥ እንደሚጠናቀቅ አብራርቷል:: ዛሬ የሱዳን መንግሥትና ሠራዊት የወረራ ግዛቱን ማስፋቱ የዚህ ስምምነት አካል ሊሆን እንደሚችል መጠርጠርም ስህተት አይሆንም:: ክቡር ሚንስትር ሆይ መቼም ይሄን የገዱ አንዳርጋቸውና የአብይ አሕመድ ስምምነት ነው ብለው እንደማያልፉት ተስፋ አደርጋለሁ:: ተስፋዬ ከንቱ ምኞት ሊሆን እንደሚችል ደግሞ የ1995 ዓ.ም. ታሪኮ ይነግረኛል:: ለሱዳን ስለሰጡት የደለሎ መሬት ተጠይቀው ‹‹በእነ አባይ ፀሃዬ መሪነት የቃል ስምምነት ከሱዳኖች ጋር ተደርጓል:: ፎርማውን አላውቅም:: ያን ጊዜ የክልል አመራር ነኝ:: የክልሉ መንግሥት በፌዴራል ጉዳዮች ላይ የመፈረም ስልጣንም የለውም::›› ያሉትን አስታወሱ ወይ? የኢትዮ ሱዳን ጉዳይ ከእርስዎ አልሸሸ አለ:: ይኸው ታሪክ መልሶ በውጭ ጉዳይ ሚንስትርነት አመጣዎ:: እርስዎ ባይዘነጉትም ይች ደብዳቤ ግልፅ ስለሆነች እስኪ ለሊጋ ካድሬዎችዎ ታሪኩን እናስታውሳቸው፡-

## በ1995 ዓ.ም. ለሱዳን የተሰጠው የኢትዮጵያ መሬት

በ1988 ዓ.ም. የወቅቱ የግብፅ ፕሬዚደንት በአዲስ አበባ የግድያ ሙከራ ተደረገባቸው:: ሙከራውን ያደረጉት ቴረሪስቶች ደግሞ በሱዳን መንግሥት ድጋፍ ተደርጎላቸው ሱዳናውያን ጭምር የተሳተፉበት ሱዳናውያን ነበሩ:: ወንጀለኞች ከመያዝና ከመደምሰስ ያመለጡት ቴረሪስቶች ሩጠው ወደ ሱዳን ሀገራቸው ገቡ ፤ ሱዳን:: የኢትዮጵያ መንግሥት የግድያ ሙከራውን ያደረጉት ግለሰቦች እንዲሰጡት ቢጠይቅም የሱዳን መንግሥት ዜጎቹን አሳልፎ እንደማይሰጥ ተናገረ:: በዚህ ምክንያ በዚያው አመት የኢትዮጵያና የሱዳን ጦርነት ተደረገ:: በኢትዮጵያ አሸናፊነትም ተጠናቀቀ:: የደርግ መንግሥት ተወግዶ ሕወሓት/ኢሕአዴግ ወደ ሥልጣን ሲመጣ ሱዳናውያን በጎንደር በኩል የኢትዮጵያን መሬት ተቆጣጥረው ነበር:: ይህንን ለማድረግ ሁለት መልካም አጋጣሚዎችን ተጠቅመዋል:: 1ኛው ሕወሓት ወደ ሥልጣን እንዲመጣ ሱዳን ታግዘው ስለነበር ያለፈ ውለታዋ የኢትዮጵያን መሬት እንድትወስድ አስችሏታል:: 2ኛው ኢትዮጵያ የመንግሥት ለውጥ መደረጉን ተከትሎ አለመረጋጋት ላይ ስለነበረች ለሱዳን አመቺቷታል:: ሀገሪቱ በሽግግር መንግሥት የምትመራበትና በርካታ ነገሮች ፈርሰው እንደ አዲስ የሚገነቡበት ጊዜ ስለነበር ለሱዳን አመቺ ነው አመቺ ሁኔታን ፈጥሮላት ነበር:: በየጊዜው የሚጮሁ ምሁራን ሁሉ ተገልለው ፊደል ያልቆጠሩ ወያኔዎች ጠመንጃ እያንቀጫቀጩ በዋና ዋና የሀገሪቱ ተቋማት የሚዘዋወሩበት ጊዜ ነበር:: ታዲያ በዚህ ጊዜ ሱዳን ወራው የነበረውን መሬት በ1988ቱ ጦርነት ለቀቀች:: ሱዳን በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ተቃዋሚዎችን የመደገፍ ልምዷ ከፍተኛ ነው:: ሕወሓት ተቃዋሚ በነበረ ጊዜ ትደግፊው እንደነበረው ሁሉ ተገልብጣ የሕወሓትን ተቃዋሚዎች ደግሞ መደገፍ ጀመረች:: ጥቂት የማይባሉ ተቃዋሚዎች ሱዳን ውስጥ እየመሸጉ ሕወሓትን ለሥልጣኑ አሰጉት:: ቀጥሎም ሁለቱ ሀገራት በምስጢራዊ ድርድር ተስማሙ:: በዚህ ሂደት ተለዋዋጩ የሱዳን ባህሪ በርካቶችን ዋጋ አስከፍሏል:: ሱዳን ግብፅ ከኢትዮጵያ ጋር የውክልና ጦርነት የምታደርግባት ሀገርም ነች:: በመሆኑም የራሷን ጥቅም እስካስከበረላት ድረስ በየጊዜው አቋሟን ትቀያይራለች:: እስስት የሆነችው ሱዳን በሀገሯ የነበሩ የኢትዮጵያ ፖለቲከኞችን ለሕወሓት አሳልፋ ሰጠች:: የመሬቷን ጉዳይም አልዘነጋችም:: በዛው በ1988 ዓ.ም. መልሳ ያጣችውን የኢትዮጵያ መሬት እንዲመለስላት ጠየቀች:: ወያኔ ፈቀደላት:: የኢትዮጵያ ገበሬዎችን አፈናቅላ መሬቱን ዳግም ተቆጣጠረችው:: በወቅቱ የነበሩት የመተማ

ወረዳ አስተዳዳሪ አቶ ሙሉዓለም ገሌ ጉዳዩን በመቃወማቸው ታስረዋል።

ይህ መሬት በ1995 ዓ.ም. ለሱዳን በድጋሜ ሲሰጥ የወቅቱ የኢትዮጵያ የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር ሚንስትር የሕወሓቱ አቶ አባይ ፀሃዬ ከአዲስ አበባ መተማ፣ ደለሎ ድረስ በሄሊኮፍተር ሄደው መሬቱን አስረከቡ። በአስር ሺህዎች ሄክታር የሚቆጠር ማለትም አብዛኛው የደለሎ መሬት ተሰጠ። በዚህም ብዙ ኢትዮጵያውያን ተፈናቀሉ። በተለይም ዘለቀ እርሻ ልማት ተወገደ። በ2000 ዓ.ም. ላይም ሌላ ተጨማሪ መሬት ለመስጠት እንቅስቃሴ ተጀምሮ በሕዝብ ተቃውሞ ሳይሳካ ቀርቷል። አቶ አባይ እንደ መለስ ዜናዊ በእንባ የመሸኘት እድል ጠሞባቸው፣ እንደ ስብሃት ነጋ ወህኒ ቤት ውስጥ መቀመጥም ከፕላኔት ሆቴል በላይ ውድ ሆኖባቸው የሱዳን ወታደሮች በእሳት እንዳቃጠሏቸው የጉልበት ሠራተኞች ደመ ከልብ ሆነዋል። አቶ ደመቀ ለእርስዎ ግን ታሪክ ዳግም እድል ሰጥቶዎታል። የማራን ሕዝብ ባይክሱ፣ ንስሀ መግባት ባይችሉ እንኳን እየሄዱበት ካለው የዳግም ስህተት መንገድዎ እንዲገነጠሉ እመክሮታለሁ።

## ክህደትዎ

‹የኢትዮጵያ መሬት ለሱዳን እንዲሰጥ የእርሶም እጅ አለበት ወይ› የሚል ጥያቄ ቀርቦሎት መልሰዋል። እንዲህም አሉ፡- «እኔ በወቅቱ ‹ፊርማ ፈረምህ› በተባልኩበት ጊዜ እንግሊዝ ሃገር ለትምህርት ሄጀ ነበር። በዚህ ጉዳይ ላይ እጀ የለበትም። እኛ በሪፖርታችን መሠረት የድሮ መሬታቸው ነው የተመለሰው ብለናል። (የሱዳኖች ማለት ነው) እዚያው እንጨት ለቅሞና ከብት ጠብቆ ያደገው ሕዝብ ‹አይደለም› ይለናል። ይሄ የደረቅ ፖለቲካ ነው። ከጓንግ ወዲህ ማዶ ሱዳኖች የኢትዮጵያን መሬት እንደያዙ ኗሪዎች ነገሩን። በእነ አባይ ፀሃዬ መሪነት የቃል ስምምነት ከሱዳኖች ጋር ተደርጓል። ፊርማውን አላውቅም። ያን ጊዜ የክልል አመራር ነኝ። የክልሉ መንግሥት በፌዴራል ጉዳዮች ላይ የመፈረም ሥልጣንም የለውም።»

እርስዎ ይህንን ቢሉም መሬቱ በ1995 ዓ.ም. ለሱዳን ከመሰጠቱ አንድ ዓመት ቀድሞ የድንበር ኮሚሽን ተቋቁሞ ነበር። በወቅቱ እርስዎ ዐማራ ‹ክልል› ሲል ሕወሓት ለሰየመው አካባቢ የአስተዳድርና ፀጥታ ቢሮ ሓላፊ ነበሩ። የድንበር ኮሚሽኑ መሥራች አባልም ነበሩ። የኢትዮ ሱዳንን ድንበር የሚወስነውና መሬቱ ለሱዳን ስለ መሰጠት አለመሰጠቱ የሚወስነውም ይኸው ኮሚሽን ነው። ስለዚህ የክልል አመራር በፌዴራል ጉዳዮች ላይ የመፈረም ስልጣን እንደሌለው የገለፁበት አመክንዮ ፉርሽ ይሆናል። ምክንያቱም የድንበር ኮሚሽኑ በፌዴራል ደረጃ የተቋቋም ነውና።

«እጀ የለበትም። አልፈረምኩም።» ቢሉም መሬት በእነ አባይ ፀሃዬ ሲሰጥ ግን ያውቁ እንደነበር አልሸሸጉም። ስለዚህ መሬት የወቅቱ የመተማ ወረዳ ዋና አስተዳዳሪ አቶ ሙሉዓለም ገሌ በ1996 ዓ.ም. ከብአዴን ተባርረዋል። ታስረዋል። ከዚህኛው አስተዳዳሪ በፊት የነበሩት የወረዳው አስተዳዳሪ ኮሎኔል ደሳለኝ አንዳርጌ ሽፍታ ተብለው በሱዳን መንግሥት ቲሃ የተባለች የሱዳን ከተማ ድረስ ታፍነው መወሰዳቸውን በአንድ ወቅት ይፋ ባደረጉት የፅሁፍ ሀተታ ምስክርነታቸውን ሰጥተዋል። በኋላም በትምህርት ምክንያት አስተዳዳሪነታቸውን ለቀዋል።

በዚህ ጊዜ እርስዎ የ‹ክልሉ› ከፍተኛ አመራር ኖት። የፓርቲውም ጭምር። የወረዳው አስተዳዳሪዎች ሲፈራረቁ ከሕዝቡ ጋር በመሆን ለበላይ አመራሮች ጉዳዩን ያሳውቁ እንደነበር ተናግረዋል። የበላይ አመራር ከተባሉት መካከል የአስተዳደርና ፀጥታ ጉዳዮች ሓላፊው አቶ ደመቀ ጉዳዩ ቀድሞ እንደሚደርስዎት አያጠራጥርም። ታዲያ ለምን መሪ ከሆኑ በወቅቱ የሕዝብን ጥያቄ ሰምተው የሀገሪቱን ሉዓላዊነት አላስከበሩም? ለምንስ የሚመሩትን የዐማራን ሕዝብ ደህንነት አላስጠበቁም? ተባባሪ አልነበሩም ወይ? በዚህ ጉዳይ እጀ የለበትም ማለትስ ምን አይነት ክህደት ነው? የሕዝብ መሪ እኮ ኖት። ዋናው ወንጀል ሕዝቡን አሳልፈው መስጠትዎ እና ሉዓላዊነትን በማስደፈሩ ጉዳይ ተባባሪ መሆንዎ አይደለምን? በጉዳዩ ከተስማሙ የወረቀት ፊርማውን ፈረሙስ አልፈረሙስ ምን ይፈይዳል?

ይህ የደለሎ መሬት አሁንም ድረስ በሱዳኖች እንደተያዘ ነው። ባለፈው ግንቦት ተሰጠ የተባለው ለም የእርሻ መሬት ደግሞ ሱዳን በአባይ ግድብ ላይ ያላትን አቋም ለኢትዮጵያ በሚደግፍ መልኩ እንድታደርገው የታሰበ መሆኑን አቶ ገዱ አንዳርጋቸው ውጭ ጉዳይ ሚንስትር በነበሩበት ጊዜ ነግረውናል። «ከሱዳን ጋር ያለንን ግንኙነት በተለየ ዲፕሎማሲያዊ መንገድ ነው የምናየው። ምክንያቱም የአባይ ግድብ ከሱዳን ጋር አወዳጅቶናል። በሱዳን ላይ ጦርነት መክፈት አንፈልግም።» ሲሉ ነበር የተናገሩት። ይህ የተንበርካኪነት ዲፕሎማሲ አይመስሎትም?

ከላይ ካስታወስሆት ንግግር ለመረዳት የሚቻለው ትክክለኛ ድንበሩን እንደማያውቁት ነው። ወይም እያወቁ አላዋቂ ለመምሰል ሞክረዋል። ያም ሆነ ይህ ወግ ደርስዎት የኢትዮጵያን ጥቅም ለማስከበር ከሱዳን ጋር የሚደራደሩ ከሆነ ሊጠቅሞት ይችላልና ጥቂት የታሪክ ማጣቀሻዎችን እንቃኝ፡- በአሁኑ ጊዜ በአካባቢው የሚኖረው ኢትዮጵያዊም ሆነ የተለያዩ ጸሐፊዎች የሚስማሙበት የሀገራቱ ድንበር ጓንግ ወንዝ ነው። ነገር ግን አንዳንድ ነገሥታት ከወንዙ ወዲያ ማዶም የኢትዮጵያ ግዛት አካል አድርገው ይገዙት እንደነበር ታሪክ ይመሰክራል። ለአብነትም ከ1624 ዓ.ም. እስከ 1659 ዓ.ም. ድረስ የነገሱት አፄ ፋሲል ይጠቀሳሉ። የዛሬው የሱዳን ከተማ ስናር ድረስ በመሄድ አስገብረው እንደነበር ‹የኢትዮጵያ የ5ሺህ ዓመት ታሪክ ከኖኅ እስከ ኢሕአዴግ› የተሰኘው የፍስሐ ያዜ መጽሐፍ ይገልፃል። እንደራሴያቸውን ንጉሥ ጊዮርጊስን በሚያስገብሩት አካባቢ ሹመዋቸው ተመልሰዋል። ሱዳንን ማስገበራቸውን በተመለከተም አዝማሪ እንዲህ በማለት ገጥሞላቸዋል፡-

«ጎንደር ቢያጉረመርም ፋሲል ፈረስህ፣

ኑብያና ስናር ወርቁን ጫኑልህ።

ሳሩን ተጠየፈ የፋሲል ፈረሱ፣

ክምር የሱዳን ወርቅ ገፈራው ነው ለእርሱ።»

በተመሳሳይ አፄ ቴዎድሮስም ወዲያ ማዶ ተሻግረው ከሰላ ላይ የጦር መንደር መሥርተው ነበር። በአንፃሩ ሱዳኖች በተደጋጋሚ ኢትዮጵያን ለመውረር የሚዳዱት እንግሊዛዊው ቅኝ ገዢቸው ሻለቃ ግዎይን ድንጋይ እየካበ ያሰመረውን መስበር ተከትለው ነው።

እየተሻሻለ ያለው የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ‹ቋሚ ጠላትም ሆነ ቋሚ ወዳጅ የለም› የሚል እንደሆነ ጠቅላይ ሚንስትሩ ‹መደመር› ባሉት መጽሐፋቸው ገልፀዋል። ወትሮም እውነት የራቃቸው አለቃዎ ይህንን ቢሉም ግብፅ ከአባይ ተፈጥሮ ጋር አብራ የተፈጠረች ቋሚ የኢትዮጵያ ጠላት ነች። ይህንን ደግሞ በሱዳን በኩል እያስፈፀመች ነው። እዚህ ላይ እንደ ሱሌማን ደደፎ አይነት ፀረ ኢትዮጵያ አምባሳደሮች ሲጨመሩበት ጦሱን ያንረዋል። የሕይዎት ዘመን ያፖለቲካ ርዕዮታቸው ዐማራን በመጥላት ላይ የተመሠረተው የኢሳያስ አፈወርቂ ካርቴምና አዲስ አበባ መመላለስም ጦሱ ገና መቼ ተጀመረ ያስብላል።

ከቡር ውጭ ጉዳይ ሚንስትር ሆይ፣ በአጠቃላይ ሱዳን ይፋዊ ወረራ ላይ ነች። ይህን በስሙ መጥራትና መመከት ያስፈልጋል። የማራን ሕዝብ ሁለት ጊዜ አይግደሉት። በኦሕዴድ/ብልፅግናነት ሌላ ትውልድ መግደል አይጠበቅቦትም። በወያኔ/ብአዴንነቶ አንድ ትውልድ ገድለዋል፣ የዘለቀ እርሻ ልማት ትውልድ። አንድ ትውልድ ስንት ነው የሚል ቆጠራ ውስጥ እንደማይገቡ እገምታለሁ። ብዙዎች የእርሻ መሬቶቻቸውን ተነጥቀው ሎተሪ አዟሪ እንደሆኑ ለማወቅ እንደ እኔ የአርቲስት ፋሲል ደሞዝን ቃለ መጠይቅ መስማት የሚጠበቅብዎት አይመስለኝም። ፋሲልን ካነሳሁ አይቀር ‹አረሱት› የሚለውን ዘፈን በደንብ ያዳምጡልኝ። በተረፈ ይችን ደብዳቤ ስፅፍሎት ለሕገ ወጥ መንግሥትዎ እውቅና የሰጠሁ እንዳይመስሎት። ከቻሉ ሥልጣን ይልቀቁ፣ ካልቻሉ የሚገዙት ሕዝብ እንዳያጡ ከወራሪ ይጠብቁን ነው ምክሬ።

ባልደራስ

ለእውነተኛ ዲሞክራሲ


ኢትዮጵያ ዳግም
የህሊና እስረኞች
ቤት እንድትሆን
መፍቀድ የለብንም!
ባልደራስ ለእውነተኛ ዲሞክራሲ